ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ ፅሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በጅማ ዞን በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በ

ነቢዩ ሐረገወይን

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ነሐሴ 2008 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ ፅሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በጅማ ዞን በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በ

ነቢዩ ሐረገወይን

አማካሪ

ዶ/ር አቢይ አሰፋ

ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ነሐሴ 2008 ዓ.ም

## አጠቃለሎ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ እና በኦሞናዳ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን እንደሚመስል እና እንዴት እንደሚዘጋጅ መተንተን ዓይነተኛ ዓላማው ነው፡፡ ጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ተንተርሶ ገላጭ የምርምር ስልትን መነሻ በመጠቀም አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም በሰነድ ፍተሻ፣ በቃለ-መጠይቅ እና ምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በክለሳ ድርሳናት ውስጥ በተጠቀሱ ተመራማሪዎች ሀሳብ ጥንካሬን እንዲያገኝ በማድረግ ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የተለያዩ ችግሮች እንዳሉበት ለማየት ተችሏል፡፡ ከችግሮቹ ውስጥም ዋና ዋናዎቹ ከአንድ አላማ በላይ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ማቀድ፣ ለክፍለ ጊዜው ይመጥናል ተብሎ የታቀደው ዕቅድ በአግባቡ ተተግብሮ አለመጠናቀቅ፣ መምህራን ባቀዱት ዕቅድ መሰረት እንዳይተገብሩ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል እና ለቋንቋው ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን የወጣውን እቅድ ከዳር ለማድረስ አዳጋች መሆኑን ፤የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበትና የራሳቸውን ግላዊ ጥላቻ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው፣ ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንጻር በተሰጠው ጊዜ በትክክል መጠቀም አልቻሉም፡፡ ከዚህም በተነሳ እቅዱን በአግባቡ መተግበር እንዳልተቻለ ከጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መምህራን በሚያዘጋጁአቸው የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚነድፏቸው የትምህርት ዓላማና ይዘቶች ውስንና በአንድ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ የሚችል ሆኖ ቢዘጋጅ፤ የአማርኛ ቋንቋን ዕቅድ አዘገጃጀትን እና አተገባበርን በተመለከተ ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ የሆነ ስልጠና በየጊዜው እያዘጋጁ ለመምህራን ስልጠና ቢሰጡ ፤መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርትን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያስችልና ተማሪን በንቃት ሊያሳትፍ የሚችል ተለዋዋጭ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴን ለመጠቀም የዕቅድ አዘገጃጀታቸውን ተለዋዋጭ ቢያደርጉ ፤የሚሉትን ሃሳቦች በመሰንዘር ጥናታዊ ስራው ተጠናቋል ፡፡

I

## ምስጋና

በመጀመሪያ የረዳኝን የሁሉም ነገር ጀማሪና ፈጻሚ የሆነውን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ በማዘጋጅበት ወቅት ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት፣ እርማት በመስጠትና አቅጣጫ በመጠቆም ስራዬ እንዲሳካ ላደረጉት ውድ አማካሪዬ ዶ/ር አቢይ አሰፋ እንዲሁም ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ የላቀ ምስጋናዬን በትህትና ከልቤ አቀርባለሁ፡፡

ጥናታዊ ጽሑፌን በኮምፒውተር በመጻፍና ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግና በማበረታታት ከጎኔ ላልተለየሽው ወ/ሮ ነፊሳ በሽር ውለታሽ ታላቅ ነውና ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡

ስራዬ የተሳካ ይሆን ዘንድ በሚያስፈልገኝ ነገር ሁሉ ከጎኔ በመቆም እና መንፈሳዊ ብርታትን በመለገስ እስከ መጨረሻው ድረስ ላበረታታሽኝ ውድ ባለቤቴ አበባ መኮንን እና አባታችን በርታ እያላችሁ ስታበረታቱኝ ለነበራችሁት ልጆቼ ኤዶም ነቢዩ፣ ፌበን ነቢዩ እና ይቤላ ነቢዩ አብሮነታችሁ ታላቅ ነበርና ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

በመጨረሻም በዩኒቨርሲቲ ቆይታችን ውስጥ የማልረሳችሁ የክፍል ጓደኞቼና በተለይም የቅርብ እና የልብ ጓደኛዬ አሰፋ በቀለ በአብሮነታችን ወቅት ድጋፍህ ከፍ ያለ በመሆኑ ሁሌም አልዘነጋህምና ምስጋናዬን ተቀበል፡፡

ማውጫ


ይዘት ገፅ

አጠቃሎ----------------------------------------------------------------------------------------------------I

ምስጋና----------------------------------------------------------------------------------------------------II

ማውጫ----------------------------------------------------------------------------------------------------III

ሙዳዬ ቃላት---------------------------------------------------------------------------------------------VII

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------------------1

1.2. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ--------------------------------------------------------------------2

1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ----------------------------------------------------------------3

1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች-----------------------------------------------------------------------3

1.5. የጥናቱ አላማ ------------------------------------------------------------------------------4

1.5.1. የጥናቱ ዋና አላማ ------------------------------------------------------------------4

1.5.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ-----------------------------------------------------------------4

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ---------------------------------------------------------------------5

1.7.የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------5

1.8. የጥናቱ ውስንነት--------------------------------------------------------------------------5

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት--------------------------------------------------------------------------6

2.1.1 ስርአተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርት------------------------------------------------------6

2.1.2. የትምህርት ዕቅድ ምንነት ----------------------------------------------------------7

2.1.3. የትምህርት ዕቅድ ከመነደፉ በፊቴ መታወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች-----------8

2..1.4. የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት-------------------------------------------------8

2.1.5. የቋንቋ ትምህርት እቅድ ዓይነቶች -----------------------------------------------------9

2.1.5.1. አመታዊ የትምህርት ዕቅድ ---------------------------------------------------------9

2.1.5.2. የመንፈቅ አመት የትምህርት ዕቅድ ---------------------------------------------10

2.1.5.3. ወርሃዊ የትምህርት ዕቅድ ----------------------------------------------------------10

2.1.5.4. ሣምንታዊ የትምህርት ዕቅድ -------------------------------------------------------10

2.1.5.5. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ----------------------------------------------------------11

2.1.6. የትምህርት ዕቅድ ይዘቶች-----------------------------------------------------------------12

2.1.6.1. የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ------------------------------------------------------12

2.1.6.2. የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች -------------------------------------------13

2.1.6.3. በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩና የተማሪው ተግባር ------------------15

2.1.6.4. የማስተማሪያ ቁሳቁሶች -------------------------------------------------------------17

2.1.6.5. ምዘና --------------------------------------------------------------------------------------17

2.1.7. የቋንቋ ትምህርት አተገባበር -----------------------------------------------------------18

2.1.8. ጥራት ያለውን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ዋና ዋና ነጥቦች-------------------19

2.1.9. በቋንቋ ትምህርት እቅድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች -----------------------20

2.1.10. የትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚያጋጥሙ ስህተቶች---------------------------------21

2.2. የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት -------------------------------------------------------------------22

## ምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴና አካሄድ


3.1. የጥናቱ ዘዴ --------------------------------------------------------------------------------------24

3.2. የተጠኝ ናሙና አመራረጥ ------------------------------------------------------------------24

3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ ---------------------------------------------------------------24

3.2.2. የክፍል ንሞና አመራረጥ---------------------------------------------------------------24

3.2..3.. የመምህራን አመራረጥ -------------------------------------------------------------25

3.2..4. ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ ናሙና አመራረጥ ---------------------------------25

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ -----------------------------------------------------------------26

3.3.1 የመዛግብት ፍተሻ -----------------------------------------------------------------26

3.3.2 ምልከታ-----------------------------------------------------------------------------------26

3.3.3. ቃለ መጠይቅ ---------------------------------------------------------------------------27

3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ -------------------------------------------------------------------------28


## ምዕራፍ አራት የመረጃ አቀራረብና ትንተና


4.1 የተጠኝዎች ግላዊ መረጃ-------------------------------------------------------------------30

4.2. መረጃ ትንተና እና ገለጻ----------------------------------------------------------------------31

4.2.1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ ሰነድ ፍተሻ ትንተና----33

4.2.2 የትምህርት ዕቅድ ይዘት ትንተና-------------------------------------------------------46

4.2.3. ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና----------------------------------------------47

4.2.4. ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና------------55

4.2.5. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት አቅርቦት ዘዴ--------------------------------63

4.2.5.1. የመምህራኑና የተማሪው ተራክቦ--------------------------------------------------64

4.2.5.2. የትምህርት ዕቅድ ግምገማ-------------------------------------------------------64

ምእራፍ አምስት

5. ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች------------------------------------------------------------66

5.1.ማጠቃለያ-----------------------------------------------------------------------------------67

5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች-------------------------------------------------------------------------69

ዋቢ መፅሐፍት ---------------------------------------------------------------------------------71

አባሪዎች

አባሪ አንድ፡ ለመምህራን የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ

አባሪ ሁለት፡ ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ ቅጽ

አባሪ ሦስት፡ ለክፍል ምልከታ ከተዘጋጀ ቅጽ የተገኙ ምላሾችን የሚያሳይ መረጃ

አባሪ አራት፡ ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ ፕሮግራም

አባሪ አምስት፡ በናሙናነት የተወሰደ ቃለ መጠይቅ

አባሪ ስድስት፡ በናሙናነት የተመረጡ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች

## ሙዳዬ ቃላት

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ ፅሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**ሙዳዬ ቃላት**

| | |
|---|---|
| Lesson Plan | የትምህርት ዕቅድ |
| curriculum | ስርአተ ትምህርት |
| syllabus | መርሃ ትምህርት |
| Cognitive domain | አእምሮታዊ ዘዴ |
| Affective domain | ስሜታዊ ዘዴ |
| psychomotor domain | ባህርያዊ ዘዴ |
| Introduction | መግቢያ |
| presentation | አቀራረብ |
| Stabilization | ማጠናከሪያ |
| Evaluation | ምዘና |

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የትምህርት ዕቅድ ምንነትን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን እንደየአመለካከታቸው ሰንዝረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በጥቂቱ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

Harmer (1983፡218) "ጥሩ መምህራን የሚባሉት በክፍል ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በጥንቃቄ የሚያስቡና እንዴት አድርገው የማስተማር መማሩን ሂደት ማደራጀት እንዳለባቸው የሚያቅዱ ናቸው" ይላሉ፡፡ እንደምሁሩ አባባል ማንኛውም መምህር ተማሪዎች ቀደም ሲል ምን አላቸው? አሁን ምን ልስጣቸው? ወደፊትስ ምን ያስፈልጋቸዋል? ብሎ ማሰብ ይኖርበታል፡፡

Cross (1991፡138) እንደሚሉት ደግሞ "በአግባቡ የታቀደ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በግልፅ የተዘጋጀ የትምህርት እቅድ መምህሩ ዘና ብሎ በራስ በመተማመን እንዲያስተምር ይረዳዋል አንዱን ተግባር ጨርሶ የሚቀጥለውን እንዲያከናውን ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ተግባራት በተወሰነላቸው ጊዜ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ያገለግላል" ይላሉ፡፡

Clarc and stars (1986፡174-175) በበኩላቸው "በአንድ ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎች የሚቀርብ ትምህርት በአጠቃላይ ስርዓተ ትምህርት ለሚሰጠው ትምህርትና በትምህርት ውስጥ ለሚገኙ ምዕራፎችና ንኡሳን ክፍሎች እንደ "አቶም" ሊቆጠር ይችላል፡፡ በየክፍለ ጊዜው የሚቀርበው ትምህርት ውጤታማነት ለአጠቃላይ ትምህርት ግብ መቺነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

አንድ መምህር ለተማሪዎች ውጤታማ የሆነ እውቀት ለማስጨበጥ ግብ መቺ ለመሆን የማስተማር ሂደቱን ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ትምህርቱን ከየት መጀመር እንዳለበት ማወቅና የተማሪውን የማወቅ ደረጃ ሊለካ በሚችል መንገድ የተለያየ የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በእውቀት ማነጽ አለበት Borich (1988፡110 እና 117-128)፡፡ ይህ

የመማር ማስተማሩ ግብ የሚሳካው መምህሩ ተጨባጭና ተግባራዊ የሆነ ውጤታማ ስራ ለመስራት ለሚያስተምረው ትምህርት የተዘጋጀውን የአጠቃቀም ሁኔታ የቅደም ተከተሉን ፍሰት በመጠቀም ራሱን ማዘጋጀት ሲችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ በቋንቋ ትምህርት እቅድ ዝግጅት ላይ ትኩረት በማድረግ ዝግጅቱን ግብ መቺ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Elizzabeth (1982፡12) ስለ ትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ ሲያስረዱ "አጠቃላይ የትምህርት አካሄድ በእቅድ ላይ የተመሰረት በመሆኑ እቅድ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ይኖረዋል" ይላሉ ፡፡ይህ ማለት በዕቅድ ያልተደገፈ ትምህርት ውጤታማ አለመሆኑን ያስረዳናል፡፡

Dorothy (1985፡48) በተጨማሪ የትምህርት እቅድን በተመለከተ ሲናገሩ "የትምህርት እቅድ ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ሂደት እንደ መሳሪያ ወይም መርጃ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለጥሩ የማስተማር ሂደት አስፈላጊና እንደመርህም ይጠቅማል" ይላሉ፡፡

እንደ እነዚህ ምሁራን አገላለፅ የትምህርት እቅድ ለትምህርት ስራ ስኬት መርህ ነው፡፡ በመሆኑም መምህሩም የመማር ማስተማር ተግባር ከመጀመሩ በፊት በእቅድ የማይመራ ከሆነ የሚጠበቅበትን አመርቂ ውጤት ላያስገኝ ይችላል፡፡ ይህ የሚያስረዳው ለትምህርት ስራ ተግባራዊ ምላሽ የትምህርት እቅድ ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም በጢሮ አፈታ ወረዳ እና በኦሞናዳ ወረዳ ውስጥ በተመረጡ አምስት ሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን እንደሚመስል በዚህ ጥናት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

ይህ ጥናታዊ ስራ የተከናወነባቸው ወረዳዎች በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ከሚገኙት ወረዳዎች ውስጥ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ለጥናታዊ ስራው የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

ጢሮ አፈታ ወረዳ ከጅማ ከተማ በስተምስራቅ በ64 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የወረዳዋ ዋና ከተማ ዲምቱ ስትሆን በውጧም አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ይገኛል፡፡ አኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ከወረዳዋ ዋና ከተማ ዲምቱ በስተምስራቅ በ26 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሲሆን ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከወረዳዋ ዋና ከተማ ዲምቱ በስተደቡብ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ በገጠር ቀበሌ ውስጥ የተመሰረተ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኦሞናዳ ወረዳ ዉስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በወረዳዋ ዋና ከተማ የሚገኝ ሲሆን ከጅማ ከተማ በስተደቡብ በ72 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም አሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከጅማ ከተማ በስተምስራቅ በ55 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ በአሰንዳቦ ከተማ የተመሰረተ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ስራ ከላይ በተገለጹት አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተጠና ጥናታዊ ስራ ነው፡፡

### 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማካሄድ አጥኚውን ያነሳሳው ዋናው ምክንያት በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ የተለያዩ ችግሮችን አልፎ አልፎ ይመለከት ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋናው የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ ከተሰጠው የትምህርት ጊዜ ጋር አጣጥመው አለማጠናቀቅ እና የአማርኛ ቋንቋ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከተሰጠው ጊዜና ሰዓት ጋር ተጣጥሞ ያለመዘጋጀት ችግር በረጅም ጊዜ የማስተማር ልምዱ ያስተውል ነበር፡፡ በመሆኑም ለትምህርት የተሰጠው የማስተማሪያ ጊዜ ሰሌዳ ከተዘጋጀው የትምህርት እቅድ ጋር ያለመመጣጠን ወይም ሌሎች ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ጥያቄ አጥኚው ስላደረበት ከዚሁም ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ችግሮች ካሉም ነቅሶ በማውጣት ለማሳየት ጉጉት ስላደረበት ይህንን ጥናት አካሂዷል፡፡

### 1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት የሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ፡፡

- በዕለታዊ ዕቅዱ ውስጥ ያሉትን የእቅድ አካላት ተጣጥሞሽ ከዓላማ እና ከይዘት አንጻር ምን ይመስላሉ?
- መምህራን ያዘጋጇቸውን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ባቀዱበት አግባብ ይተገብራሉ?

- መምህራን ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ተግባር ለዉጦ ለመስራት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ይመስላል?
- በዕለታዊ ዕቅዱ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ዓላማ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ የሚከተሉት ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች መልስ ያገኛሉ፡፡

### 1.5.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በጢሮ አፈታ ወረዳ በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በኦሞናዳ ወረዳ ውስጥ በተመረጡ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን እደሚመስል በመፈተሸ የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ነው፡፡ በመሆኑም ይህ አጠቃላይ አላማ ከዚህ በታች ያሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይይዛል፡፡

### 1.5.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. በዕለታዊ ዕቅዱ ውስጥ ያሉትን የእቅድ አካላት ተጣጥሞሽ ከዓላማ እና ከይዘት አንጻር መለየት፤
2. መምህራን ያዘጋጇቸውን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን መተግበርና አለመተግበራቸውን መገምገም ፤
3. መምህራን ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ተግባር ለዉጦ ለመስራት ያላቸውን ተነሳሽነት ማሳየት፤
4. በዕለታዊ ዕቅዱ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ለይቶ ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የዓመቱንም ሆነ የዕለታዊ የትምህርት ወሰን በማመልከት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች የሚያበረክተው አስዋፅኦ ቀላል አይደለም፡፡ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

- በጥናቱ ለታቀፉ ትምህርት ቤቶች መምህራን በዕቅዱ ውስጥ ያሉትን የዕቅድ አካላት ተጣጥሞሽ ጠብቀው ከአሁን በፊት ከነበረው አዘገጃጀትና አተገባበር በተሻለ መልክ እንዲዘጋጁ መነሳሳትን ይፈጥራል፡፡
- ለመርሀ ትምህርትና ለስርአተ ትምህርት አዘጋጆች መነሻ ሀሳብ ይሆናል፡፡
- ከዚህ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናት ለሚያጠኑ አጥኚዎች በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኩራል፡፡ አጥኚው ከቋንቋ ትምህርት እቅድና ስፋት አንፃር ከላይ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ብቻ ተወስኖ ጥናቱን አካሂዷል፡፡ ከዚህ ርዕስ ውጭ ያሉትን የዕቅድ አይነቶች ማለትም አመታዊ፣ መንፈቀ አመታዊ፣ ወርሃዊ እና ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በዝርዝር ማየት የዚህ ጥናታዊ ስራ ትኩረት አይደለም፡፡

## 1.8. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናታዊ ስራ የሚከተሉት ውስንነቶች ይገኙበታል፡፡ አጥኚው ጥናታዊ ስራውን ለማከናወን ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ጥናቱን እስካጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተለያዩ ስራዎችን ለመዳሰስ ጥረት አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው የዳሰሳቸው ጥናታዊ ስራዎች ጥናቱ ከሚጠበቅበት ደረጃ አንጻር ተመጣጣኝ የሆኑ ጥናታዊ ስራዎችን ማግኘት አልቻለም፡፡ በመሆኑም ደረጃው ከሚፈልገው ጥናት አንጻር ተዛማጅ ስራዎችን በሚፈለገው መንገድ ማግኘት አለመቻል የዚህ ጥናታዊ ስራ ውስንነት ነው፡፡

## ምእራፍ ሁለት:-ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. ስርአተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርት

የትምህርት ዕቅድ የሚመነጨው ከስርአተ ትምህርቱና ከመርሃ ትምህርቱ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ገልጸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Musica. (1973) ስርአተ ትምህርት እንደማንኛውም የማስተማሪያ መሳሪያ ይዘት የሚቆጠር ነው፡፡ የሚል ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Cunning- Worth (1995፡54-58) “ስርአተ ትምህርት የትምህርትና ዝርዝር አላማዎችን የሚይዝ፣ የትምህርት ይዘትን የመምረጥና የማደራጀትን ቴክኒክ የሚያመላክት፣ የመማር ማስተማሩን ሂደትና ምዘናውን የሚይዝ ዕቅድ ነው፡፡” በማለት ይገልጹታል፡፡ Dubin and Olishtain (1986) በበኩላቸው ስለ ስርአተ ትምህርት ሲያስረዱ "ስርአተ ትምህርት በትምህርት ቤት የሚሰጡና ለተማሪዎች የሚሰራጩትን የትምህርት አይነቶች የተመረጡ፣ የተጣሩ፣ የተቀናጁ የትምህርት ይዘቶችን፣ ደጋፊ መሳሪዎችን፣ የመገምገሚያ ዘዴዎችን፣ ወዘተ የሚይዝ ሰነድ ነው፡፡" ሲሉ ይበይኑታል፡፡

ከላይ የተገለጸው ሀሳብ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ስርአተ ትምህርት በጣም ሰፊና ጥቅል ሀሳቦችን የያዘ ሰነድ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያየዘ ከስርአተ ትምህርቱ ስለሚመነጨው መርሃ ትምህርት ደግሞ ምሁራኑ የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ መርሃ ትምህርት በአንድ ትምህርት ተቋም በየክፍል ደረጃው የሚቀርብ ዝግጅት ሆኖ በየትምህርት አይነቱ የተቀነባበሩ ይዘቶችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የመገምገሚያ ስልቶችን የሚያመለክት መግለጫና ለመማር ማስተማር የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡፡ መርሃ ትምህርት የትምህርቱን አላማ ፣ይዘትና የማስተማር ዘዴ ከመያዙም ባሻገር ታላሚው አካል/ተማሪው ከአካባቢው የሚገኘውን የህይወት ልምድና እውቀት በመጠቀም የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚሰራበት የትምህርት ዕቅድ ነው Nunun (1988፡1-5፣ Yalden. 1987፡14-20)፡፡

መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት አይነት ወይም ክፍል ደረጃ የሚሸፍን የትምህርት ርዕስ የሚገለጽበት ነው፡፡ እያንዳንዱ በክፍል የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት የሚያስፈልገው የጊዜ ወሰን፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴና ልምምድ የሚደረግበት ሂደት በማያሻማ መንገድ የሚቀርብበት ነው Cunning-Worth (1995፡54-58)፡፡

### 2.1. 2. የትምህርት ዕቅድ ምንነት

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ተማሪዎችን ለማስተማር የታቀደውን ትምህርት ወደ ተግባር መለወጥ የሚያስችል በሳይንሳዊ ዘዴ የተዘጋጀ የስራ ማገገሚ መሳሪያ ነው፡፡ Elizzabeth (1982፡12) ስለ ትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ ሲያስረዱ "አጠቃላይ የትምህርት አካሄድ በእቅድ ላይ የተመሰረት በመሆኑ እቅድ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ይኖረዋል፡፡"

ከዚህ በተጓዳኝ Dorothy (1985፡48) ስለዚህ እቅድ ሲናገር "የትምህርት እቅድ ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ሂደት እንደ መሳሪያ ወይም መርጃ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለጥሩ የማስተማር ሂደት አስፈላጊና እንደመርህም ይጠቅማል" ይላሉ፡፡ ይህ ማለት የመማር ማስተማርን ሂደት ያለ ዕቅድ ስኬታማ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ በመሆኑም የትምህርትን ሂደት ከግብ ለማድረስ ዕቅድ ወሳኝና ዋነኛ የመምህሩ ተግባር መሆኑን ማወቅና መተግበር ተገቢ ነው፡፡

የትምህርት እቅድ ከጀማሪዎች መምህራን ጅምሮ ረጅም የስራ ልምድ አስካላቸው መምህራን ድረስ ሁሉም ይገለገሉበታል፡፡ እንደዚሁም የትምህርት እቅድ ከታችኛው የትምህርት እርከን አንስቶ እስከ ከፍተኛ የትምህርት እርከን ድረስ የሚሰራበት ወሳኝ መሣሪያ መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡ Fink, DL (2005). የትምህርትን ዕቅድ ሲገልፁ የትምህርት ዕቅድ የተቀናጀ ተለጣጣቂነት ያለው የትምህርት ዕቅድ ለታቀደው ግብ /አላማ/ በአግባቡ ለማከናወን ያስችላል ይላሉ፡፡

### 2.1.3. የትምህርት ዕቅድ ከመነደፉ በፊት መታወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች

ዕቅድ በመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ የትምህርት ዕቅድ ከመነደፉ በፊት መታወቅ ያለባቸው ዋና ዋና ነጥቦች አሉ፡፡ እነርሱንም Elizzabeth (1982፡12) እንዲህ አስቀምጠዋል፡፡ "የትምህርቱን ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ፣ በተመረጠው ይዘት ላይ ተማሪዎች የሚያውቁትን ለይቶ ማውጣት፣ የመማር ማስተማር አላማውን መዘርዘር፣ ዓላማውን ለመተግበር የሚያግዙ የመማር ማስተማር ስርዓቶችን ማዘጋጀት፣ እነዚህን ስርዓቶች መተግበርና አለመተግበራቸውን ለማስገንዘብ መወሰን የሚሉት መሰረታዊ ነጥቦች መታወቃቸው የትምህርትን ዕቅድ በጥንቃቄ ለማዘጋጀት ያግዛሉ፡፡"

የትምህርት ዓላማና ዓላማውንም በተገቢው ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ የትምህርት ይዘቶች በደንብ ተለይተው መታወቃቸው የትምህርቱን አቀራረብ ዘዴ አቅጣጫ ለማስያዝና ተግባራዊነቱንም ለመገምገም የሚስችል ፍንጭ ይሆናል፡፡ የትምህርቱ ርዕሰ ጉዳይ ከተመረጠ በኃላ በሱ መነሻነት የትምህርትን ይዘት ለመምረጥ የሚያስችሉ ነጥቦችን Lewey (1977፤67-69) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ የትምህርት ይዘቶችን ለመምረጥ ዓላማዎች አግባብነት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው፣ የትምህርት ይዘቶች ወቅታዊ መሆን እንዳለባቸው፣ ትምህርቱን የሚማረው ተማሪና አካባቢው የተጣጣሙ መሆን እንዳለባቸው፣ ትምህርቱም ከተማሪው ልምድና አካባቢ ጋር የሚዛመዱ መሆን እንዳለባቸው፣ ተማሪው በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሚማረውን በተግባር ከሚለማመዳቸው ጋር መመጣጠኑን መረዳት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህ የትምህርት ይዘቶች ከዓላማው ጋር ግንኙነት ያላቸውና ዓላማውንም ለመጨበጥ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይዘቶች የተማሪውን የአእምሮ ብስለት ደረጃ የሚመጥኑና በአካባቢ የሚገኙ ነገሮችንም መነሻ በማድረግ ሊመሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት የትምህርቱ አላማና ይዘት ከመጣጣም በዘለለ ወቅታዊነቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ ነው፡፡ ምክንያቱም ወቅታዊነቱን ያልጠበቀ የትምህርት ዕቅድ ተማሪው አካባቢውንና ልምዱን በማቀናጀት የሚፈለገውን እውቀት እንዳያገኝ የሚያግደው በመሆኑ ነው፡፡

### 2.1.4. የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት

ለጥሩ የማስተማር ሂደት ድጋፍ መሆን የሚችሉ የትምህርት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መሪ ሀሳቦችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በተለይ የዕለት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ውስጥ በዋናነት የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ የቋንቋ መምህር የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ከማዘጋጀቱ በፊት ስለ ተማሪው፣ ስለ መማሪያ ክፍሉ፣ ስለ መማሪያ መጽሐፍ ይዘትና አጠቃላይ በዕቅዱ ላይ መስፈር ስለሚገባቸው ዝርዝር ጉዳዮች ጠለቅ ያለ እውቀት ቢኖረው የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም መምህሩ አስፈላጊ የሆኑትን አቢይ ነጥቦች በጥልቀት ከተረዳ በመምህሩ ለሚዘጋጀው የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ እገዛ ሊያደርግለት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ለምን እና ምን እንዲሁም በምን ዘዴ እንደሚያስተምር አስቀድሞ እንዲያስብ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

የዕቅድን አዘገጃጀት በተመለከተ Elizzabeth (1982፡18) የሚከተሉትን መርህ ሐሳቦች አስቀምጠዋል፡፡ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ሊካተት የሚገባው ቀን፣ ክፍል፣ የተማሪዎች ዕድሜ፣ የተማሪው ብዛት፣ ክፍለ ጊዜ፣ ጠቅላላ አላማና ይህንን ርዕስ ለምን እንደሚያስተምር፣ የሚያስተምረው የትምህርቱ ይዘት ምን እንደሆነ፣ የታቀደው የትምህርት አወቃቀር እና የጊዜ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል፣ ውስን ወይም የመማር ማስተማር ዓላማ ከሚያስተምረው ትምህርት ተማሪው ምን እንደሚማር ማወቅ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ እንደ ምሁሩ አገላለጽ የቋንቋ መምህራን የትምህርት ዕቅድ ሲያዘጋጁ ከላይ የተጠቀሱትን መሪ ሀሳቦች በትምህርት ዕቅዳቸው ውስጥ ማካተት እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣሉ፡፡

### 2.1.5. የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዓይነቶች

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዓይነቶችን Callhan and Clark (1988፡64) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ "የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ መምህሩ ለተማሪው ምን ማስተማር እንደሚገባው ለመወሰን የሚያስችል ለመምህሩ ቁልፍ የሆነ መሳሪያ ነው፡፡ ይሉና በመማር ማስተማር ሂደት ለመምህሩ እንደማስተማሪያ መርጃ ሆነው የሚቀርቡ አምስት ዓይነት የትምህርት ዕቅዶች ማለትም ዓመታዊ ፣ መንፈቀ ዓመታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሳምንታዊ እና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች በመባል ይታወቃሉ፡፡" ይላሉ፡፡ይህ የሚያሳየው የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ዓይነቶችን በአግባቡ በፈርጅ በፈርጁ አቅዶ መጠቀም ተገቢ መሆኑን ነው፡፡ይሁን እንጂ ከአምስቱ የዕቅድ አይነቶች በትምህርት ቤት በስፋት እየተተገበረ የሚገኘው አመታዊው እና ሳምንታዊው/ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡

#### 2.1.5.1. አመታዊ የትምህርት ዕቅድ

ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍና የመምህር መምሪያ በጥልቀት በመመርመር ከሀገሪቱ አመታዊ የትምህርት ካላንደር ጋር ተገናዝቦ የሚዘጋጅ የዕቅድ አይነት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቅድሚያ በአመቱ ውስጥ ያሉት የስራ ቀናት በዝርዝር እንዲለዩ ይደረጋል፡፡ ያሉት የሥራ ቀናት በዝርዝር ከተለዩና ከታወቁ በኋላ በእነዚህ የስራ ቀናት ውስጥ ምን ያህል ክፍል ጊዜያት ሊኖሩ እንደሚችሉ ያሰላል፡፡

የክፍለ ጊዜያቱ መጠን በትክክል ከታወቀም በኃላ በተለይ መርሃ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ አመታዊ ክንውን በሁለት መንፈቀ አመት ተከፍሎ ጠቅለል ባለ መንገድ

እንዲሰፍር ያደርጋል፡፡ ስለዚህም የትኛው የትምህርት ርእስ መቼ እንደሚቀርብ፣ እንዴት እንደሚቀርብ፣ ምዘናው መቼ መቼ እንደሚከናወን ጠቋሚ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል፡፡

#### 2.1.5.2. የመንፈቅ አመት የትምህርት ዕቅድ

ይህ የትምህርት ዕቅድ ባጭሩ በመንፈቀ ዓመቱ ውስጥ በሚኖሩት  የክፍለ ጊዜያት መጠን ላይ ተመስርቶ ሊያከናውን  የሚፈልገውን  ትምህርታዊ ክንውን ጠቅለል ባለ መንገድ የሚያቅድበት ነው፡፡ በዚህ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ወርሀዊ ትምህርት በሚፈቅደው መሰረት መሸፈን የሚገባቸው ይዘቶች በሙሉ በጊዜ መደብ ተደልድለው ይቀመጣሉ፡፡ የመንፈቀ አመት የትምህርት ዕቅድ መሰረት የሚያደርገው መሰረታዊ ተብሎ የሚጠቀሰውን አመታዊ የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡

#### 2.1.5.3 ወርሃዊ የትምህርት ዕቅድ

ይህ የትምህርት ዕቅድ አይነት መምህሩ በወር ውስጥ በሚኖሩት የክፍለ ጊዜያት መጠን ላይ ተመስርቶ በታቀደው ወር ውስጥ ሊያከናውን የሚፈልገውን ትምህርታዊ ክንውን የሚያቅድበት ነው፡፡ በዚህ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ በሳምንት ውስጥ በሚኖሩት ክፍለ ጊዜያት መጠን ላይ በመመስረት ምንና እንዴት እንደሚከናወን የሚገልፅበት የዕቅድ አይነት ነው፡፡ ወርሃዊ የትምህርት ዕቅድ መሰረት የሚያደርገው አመታዊውንና መንፈቀ አመታዊውን የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡

#### 2.1.5.4 ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ

ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ መምህሩ በሳምንቱ ቀናት ውስጥ በሚኖሩት የክፍለ ጊዜያት መጠን ላይ ተመስርቶ በታቀደው ሳምንት ውስጥ ሊያከናውን/ሊያስተምር የሚፈልገውን ትምህርታዊ ክንውን የሚያቅድበት ነው፡፡ ይህ የትምህርት እቅድ መሰረት የሚያደርገው ወርሀዊውን የትምህርት እቅድ ሲሆን ወርሃዊ የትምህርት እቅድ በማይኖርበት አጋጣሚ ግን በመንፈቅ ዓመቱ ወይም በዓመታዊ የትምህርት እቅድ ላይ ይመሰረታል፡፡ ይህ የሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ መግለጫ ቅፅ በብዙ ትምህርት ቤቶች ይዘጋጃል፡፡ይህም የዕቅድ ዓይነት የየእለቱ ትምህርት የተወሰነ አላማ መሰረት በማድረግ በሳምንት ውስጥ በሚኖሩት ክፍለ ጊዜያት ምንና እንዴት ለማከናወን እንዳቀደ የሚገልፅበት ነው፡፡

### 2.1.5.5 ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ

እለታዊ ትምህርት እቅድ አንድ መምህር በአንድ ክፍለ ጊዜ ዉስጥ ሊያከናውነውን የሚፈልገውን የትምህርት ሂደት በዝርዝር በቅድም ተከተል የሚያቅድበት ነዉ፡፡ በዚህ የትምህርት እቅድ ውስጥ የእለቱን ያቀዳቸዉን ተግባራት በዝርዝር ለያይቶ ማስፈር የሚጠበቅበት ሲሆን የክንውኑንም ቅድም ተከተልና ለክንውኑ የተመደበውን ጊዜ ምጣኔ ማሣየት ሌላው ተግባሩ ይሆናል፡፡ htt;//gsi.berkely-edu/gsi-guide-contents/pre-semester-infro/first-day-plan/.....ድህረ ገፅ ላይ አስቀምጦታል፡፡

ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከወርሃዊ የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚዘጋጅ የዕለት ተዕለት የማስተማሪያ ዕቅድ ነው፡፡ ይኸውም መምህሩ በየዕለቱ ምን ማስተማር እንደሚገባው ዘርዝር ባለ መልኩ የሚያዘጋጀው ሲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ዕውቀት በመረጣቸው የማስተማሪያ መሣሪያ በመታገዝ በዝርዝር የሚፈለገውን እንዲገልፅ ያዘጋጁታል Ray (1969፡24)፡፡ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች ከዓመታዊና ከወርሃዊን የትምህርት ዕቅድ ካዘጋጀ በኋላ የእያንዳንዱን ቀን ዕቅድ የሚያቅድው የዕለቱን ሥራ እንዳጠናቀቀ ነው፡፡ ይኸውም በየዕለቱ የተሠራውን ሥራ በማጤን በመቀጠል ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲመረምር ይረዳዋል፡፡

የዕለቱ የትምህርት ዕቅድ አንድ የትምህርት ክፍል ጊዜ ወሰን በመሆኑ ከጊዜው መጠነ ርዕይ አንፃር መምህሩ በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ አናሳ ወይም በርካታ የማስተማር እንቅስቃሴዎችን ባለመፈፀም በጥንቃቄ መውሰድ አለበት፡፡ በአንድ ርዕስ ላይ ጠለቅ ያለውን ምርምር በማድረግ የሌለውን ጠቃሚ ጉዳይ ጊዜ ከማባከን መቆጠብ አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በቋንቋ ዕቅድ ውስጥ ዋናና ወይም መካተት የሚገባቸው የዕቅድ ክፍሎች ዓላማዎች፣ የትምህርት ማቅረቢያ ዜዴዎች፣ የመምህሩና የተማሪው ተግባር፣ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችና ምዘና ናቸው፡፡ እነዚህን አንድ በአንድ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 2.1.6. የትምህርት ዕቅድ ይዘቶች

#### 2.1.6.1. የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች

የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች በየትኛውም ደረጃ ወይም ክፍል በስርዓት መነደፍ ያለባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አንድ መምህር ለማስተማር ወደ ክፍል ከመግባቱ በፊት በየዕለቱ ማስተማር የሚገባውን ትምህርት በተመለከተ አስቀድሞ ዓላማ መንደፍ አለበት፡፡ ለተማሪው በዕለቱ ማቅረብ የሚገባውን ትምህርትና የሚጠበቅበትን የባህሪይ እና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በተገቢው ሁኔታ መነደፍ አለባቸው፡፡ አነዳደፉቸውን በተመለከተ Elizzabeth (1982፡13) ሲያስረዱ "የመማር ማስተማር ዓላማዎች መገለፅ ያለባቸው ተማሪዎች በወቅቱ የተመደበላቸውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣ የተማሩትን እንዴት መተግበር አለባቸው ከሚለው አንፃር መሆን አለበት፡፡የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ስንነድፍ ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ ተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ ማስቀመጥ እንጂ መምህሩ ምን ማድረግ እንዳለበት ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡" ይላሉ ፡፡

የትምህርት ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በግልፅ መስፈር አለባቸው፡፡ Dorothy (1985፡45) ሲያስረዱ "ዓላማዎች መገለጽ ወይም መነደፍ ያለባቸው ሊስተዋልና ሊለካ ወይም ሊገመት በሚችል መንገድ መሆን አለበት" ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በማያይዝ Ray (1969፡19) የመማር ማስተማር ዓላማ በግልፅ መስፈር እንዳለባቸው ሲያብራሩ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ የሚፃፉ ዓላማዎች ውስንና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ ወይም የተማሪዎችን የባህሪይ ደረጃ የሚገመግምና የሚያስፈልገውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሆን አለባቸው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም Ray (1969፡24) መምህሩ በሚያዘጋጀው የዕለት ተዕለት የትምህርት ዕቅድ አነዳደፍ የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስ እንዲችል ሆኖ ቢዘጋጅ ተመራጭነት ይኖረዋል ይላሉ፡፡

ዓላማዎቹ በክፍል ውስጥ የተማሪውን ፍላጎት ችሎታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ መሆናቸውን ፣ ዓላማዎቹ የተወሰኑና ከሚፈለጉት ባህሪያት ከተጠቃሚ ዕሴቶች ወይም ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያላቸው መሆኑን ፣ ዓላማዎቹ በሐሳብ ፣ በምልክት ፣ በእሴት ፣በልምድ ወይም በስሜት መገለጽ መቻላቸውን እና ለስኬማነታቸው ለተማሪው የባህርይ

ብቃት በማስገኘት በጎ/ አበረታች/ የባህሪይ ለውጥ በማምጣት የሚረዱት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

#### 2.1.6.2. የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች

መምህሩ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ጠለቅ ያለ ብቃት ቢኖረውም ያለውን ዕውቀት በሚፈለግ መልኩ ለተማሪው መግለፅ ካልቻለ ብቁ መምህር ላያሰኘው ይችላል፡፡ ይህ እንዳይሆን በተቻለ መጠን መምህሩ ጥሩ የማስተማሪያ ዜዴዎች ባለበት ቢሆን ይመረጣል፡፡

Borich (1988፡100፣ 117፣ እና 128) በተለያዩ ስልቶች መጠቀም ጠቃሚ እንደሆነ ሲገልፁ አንድ መምህር ለተማሪዎቹ ውጤታማ የሆነና እውቀት ለማስጨበጥ የማስተማር ሂደቱን ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ትምህርቱን ከየት መጀመር እንዳለበት ማጤንና የተማሪውን የማወቅ ደረጃ በሚመጥን መልኩ የተለያዩ የማስተማሪያ መንገዶችን ተጠቅሞ ተማሪዎችን በዕውቀት ማነፅ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተግባራዊ የሆነ ውጤታማ የትምህርት ሥራ ለመስራት የሚችሉ ለቋንቋ ትምህርት ዕቅድ የተዘጋጀውን የአሰጣጥ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ዜዴዎችን ተጠቅመው ተግባራዊ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች እንደ ትምህርቱ ጠባይና ባህሪይ ተለዋዋጭ ከሆነ አርኪ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ Harmer (1991፡221)፡፡ ተማሪዎች አንድ ዓይነት ለሆነና የማይለወጥ የማስተማሪያ ዜዴ በተደጋጋሚ የሚጋለጡ ከሆነ ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቅረፍ የመማር ማስተማሪያ ዜዴውን ሁልጊዜ ተለዋዋጭና ማራኪ ለማድረግ አስቸጋሪ ቢሆንም በተቻለ መጠን በተለያዩ የማስተማሪያ ዜዴዎች በመጠቀም ተማሪዎችን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተማሪዎቹ ዘንድ የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን የማከናውን ፍላጎት ሊጨምር ይችላል፡፡

ከዚህ ጋር በማያያዝ ስለትምህርት ማቅሪቢያ ዘዴዎች Harmer (1991፡225) ሲያብራሩ "አንድ መምህር በመማር ማስተማር ሂደት ዘውትር አንድን ሀሳብ በአንድ አይነት መንገድ የሚያቀርብ ከሆነ ለምሳሌ፡- ሁልጊዜ በንግግር መልክ ትምህርቱ ቢቀርብ በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ይስተዋል የነበረው የጥያቄና መልስ ምልልስ እየከሰመ ይሄዳል፡፡ የማንበብ ስልቶች ዘውትር ጥቃቅን ነገርን በማሰባሰብ ላይ ማተኮር የለባቸውም፡፡ ይህ ከሆነ

ተማሪዎቹ ሌላ ጥረት እንዲያደርጉ የማይገፋፋ ምንባብ በራሱ አሰልቺ ይሆናል፡፡ ይህ እውነት በማንበብ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በሚደጋገሙ ክስተቶች ላይ ተፈፃሚነት አለው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው" ይላሉ፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙባቸው የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች በአብዛኛው ተማሪውን በስፋት የሚያሳትፉ መሆን አለባቸው፡፡ John (1982፡14) ሲያስረዱ ተማሪዎች መማር ያላበቸው በሚሰሩት ወይም በሚያደርጉት ድርጊት መሆን አለበት ስለዚህ ይህንን ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ማቅረቢያ ዜዴዎች ሊያሰሩ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡

የትምህረት ማቅረቢያ ዘዴዎች በመማር ማስተማር ሂደት ለሚነደፉ ዓላማዎች ማስፈፀሚያ መንገዶች ናቸው፡፡ Ray (1969፡20) የትምህርት ማቅረብያ ዘዴዎች በራሳቸው ለትምህርት እልባት ሊያስገኙ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ለትምህርቱ እልባት ማስገኛ መንገዶች ብዙውን ጊዜ የትምህርት ዓላማዎች ማስፈፀሚያ ናቸው፡፡

በመምህራኑ የሚነደፉ የትምህርት ዓላማዎችን ለማስፈፀም የሚቀርቡ የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስ የሚችሉ ቢሆኑ ይመረጣሉ በማለት Ray (1969-250) የሚያቀቧቸው ዝርዝር ነጥቦች አሉ፡፡

እነርሱም፡-

1. ማስተማር ሥርዓቶችና የመማር እንቅስቃሴዎች ወደ አንድ መደምደሚያ ያመራሉን ወይንስ ግልፅ አማራጭ ያነሳሉን?
2. ሀሳብና ችሎታን ማሳየት የሚችሉ በቂ ምሳሌዎች ተካተዋልን?
3. የሚያስፈልጉ ዓላማዎችን በማስፈፀም በኩል ዘዴዎቹ ተገቢ ናቸውን?
4. በቂ የተለያዩ የመማር እንቅስቃሴዎችን በዕቅድ በመያዝና ተማሪውን? በማሠራት ተመጣጣኝ ስኬት አስገኝቷልን?
5. ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁና ግልፅ ያልሆኑ ነጥቦች ላይ እንዲወያዩባቸው ዕድል ይሰጣቸዋልን?
6. በትምህርቱ ውስጥ የቤት ሥራ መስጠት ካስፈለገ የት ላይ መሆን እንዳለበት

ይገልፃልን?

7. አንድን የትምህርት ምዕራፍ ከሚቀጥለው የትምህርት ምዕራፍ ጋር ያለውን ተገቢ ግንኙነት እንዴት ማዛመድ ይቻላል?

8. በሥነ ሥርዓት በኩል የታዩ ችግሮች አሉን እነዚህን ችግሮች እንዴት መከላከል ይችላል?

9. የመማር ሥርዓቱን ዓይነትና ተከታታይነት በመጠበቅ ረገድ የዓላማው ይዘቶች ከግንዛቤ ገብተዋል?

10. በአንድ በተለያዩ ክፍል ውስጥ ቢያንስ በከፊል የተለያዩ ፍላጎቶችንና ችሎታዎችን ማምጣት ችለዋል?

11. አዲስ ርዕስ ለተማሪዎቹ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎቹ ከነበራቸው ልምድ በመነሳት አስተያየት እንዲሰጡበት ዕድል ይሰጣቸዋልን?

ከላይ የተዘረዙትን የትምህርት ማቅረብያ ዜዴዎችን መሠረት አድርጎ የተነደፈ የመማር ማስተማር የትምህርት ዕቅድ የትምህርቱን ዓላማ ለማስፈፀም ብቃት እንዲኖረውና የትምህርቱንም ሂደት ውጤታማ ሊያድረገው ይችላል፡፡

### 2.1.6.3. በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩና የተማሪው ተግባር

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና በጊዜውና በወቅቱ ለተማሪዎቻቸው የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት ማሳወቅ ነው፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት እያንዳንዱ ተግባር በተማሪዎቻቸው ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡ ምክንያቱም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ሞዴሎች ናቸው፡፡ ተማሪዎችም ከመምህራኑ ጎን በመሆን በየዕለቱ ለሚሰጣቸው የክፍል ውስጥ ትግበራ አስፈላጊ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ያለበለዚያ መምህሩ ብቻውን የክፍል ውስጥ ትግበራ የሚያከናውን ከሆነ ተማሪዎች አመርቂ የሆነ ውጤት አያመጡም፡፡

መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡት ትምህርት እንዴት በቅደም ተከተል በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ማስፈር እንዳለባቸው Grant (1991፡80) ሲያስረዱ መምህራን

በየዕለቱ በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ትምህርት በተመለከተ ዕቅዳቸው ላይ ሲነደፉ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎችን ቢከተሉ ይመረጣል፡፡

በመጀመሪያ የዕለቱን ትምህርት ለተማሪዎቻቸው ማስተዋወቅና ተማሪዎቹ የትምህርቱ ፍላጎት እንዲያድርባቸው እና በንቃት እንዲከታተሉ ማነቃቂያ ማድረግ ስለአቀረቡት ርዕስ ራሳቸው አስቀድመው ማብራሪያ ከመስጠታቸው በፊት ተማሪዎቹ ስለ ርዕሱ ቀደም ያለ ዕውቀት እንዳላቸው ዕድል በመስጠት መጠየቅ በመጨረሻም በሚያቀርቡት የዕለት ትምህርት ውስጥ ሙያ ነክ ቃላት ወይም ከባድ ቃላት ናቸው ብለው የሚያምኑበትን ማስተማር ናቸው፡፡ የቃላት ፍቺው ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት አንዳንድ የመደናገርና የመረዳትን ችግር በተማሪዎቹ ላይ እንዳይከሰት ለማድረግ ይረዳሉ፡፡

የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ በቤታቸው ተማሪዎቻቸው እንዲሠሩ የሚፈልጉትን ማናቸውንም ተግባር ራሳቸው በደንብ የሚያወቁት መሆን አለበት፡፡ Harmer (1991፡221) "መምህራን ተማሪዎቻችው እንዲፈፀሙላቸው የሚፈልጉትን ማንኛውም ክሂል አስቀድመው እራሳቸው ቢቻል በተግባር አሊያም በቲዎሪ ደረጃ ሊያውቁት ይገባል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ ማመልከቻ መጻፍ የማይችል ከሆነ ተማሪዎቻቸው እንዲፅፉ ማድረግ ይጠቅማል፡፡"ይላሉ፡፡

መምህራን በዕቅዳቸው ላይ ከተማሪዎቻቸው ብቃት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ ተግባር ለማዘጋጅት እንዲረዳቸው የተማሪዎቻችውን ችሎታ አስቀድመው የሚያውቁ ቢሆን ይመረጣል በማለት Dorothy (1985.51) የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡"በይበልጥ መምህራን ስለ ተማሪዎቻቸው አስቀድመው ካወቁ በጥሩ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን እያዝናኑ የማስተማር ስልት የማስተማሩን ሂደት የሚያጎለብት መሆን አለበት፡፡"ይላሉ፡፡

Hargreaves (1972፡135-136) ሲያስረዱ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት የአመራር ብቃት በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን ዕድገት በማፋጠን አኳያ ትልቅና ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ዲሞክራት መምህራን ተማሪዎቻቸው በነፃነት ሐሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታታሉ፡፡ በተጨማሪም አንድን ተማሪ ከሌላው ባለማበላለጥ ያከብራሉ፡፡ ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡

እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን የውስጥ ስሜት እንዲናገር ዕድል ይሰጣሉ፡፡ ይህም በራሳቸው ላቅ ያለ አመለካከት እና በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩ ያደርጓቸዋል፡፡

### 2.1.6.4. የማስተማሪያ ቁሳቁሶች

የቋንቋ መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው መሠረት ለሚፈፅሙት ተግባር የማስተማሪያ መረጃ መሣሪያዎችን ቢጠቀሙ የመማር ማስተማሩን ሂደት ቀልጣፋ ከማድረጉም በላይ ትምህርቱን ለማስተማር ቀላል ያደረጓቸዋል፡፡ Sells (1981፡268) በመማር ማስተማር ሂደት ስለማስተማሪያ ቁሳቁሶች አስፈላጊነት ሲገልፁ ለትምህርት መስጫነት የተለያዩ ዓይነት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በትምህርት ሂደት ላይ መሠረታዊ ምርምርን ይፈጥራሉ፡፡ ሀሳቡን ይሰበስባሉ፡፡ ፍላጎትን ይቀሰቅሳሉ፣ መረዳትን ይጠናከራሉ፣ ዝምድናን ያፀናሉ፣ ትዝታን ይፈጥራሉ፣ ሀሳብን ያነሳሳሉ በተጨማሪም የምንማረውን ትምህርት በማጠናከር ጊዜንና ሀይልን ይቆጥባሉ ይላሉ፡፡

የቋንቋ መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ጥሩ የማስተማሪያ ቁሳቆሶችን ማስፈራቸው ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በተገቢው ጊዜና ቦታ የመጠቀምና የተነደፈውን የመማር ማስተማር ዓላማ ግብ ማስገኘት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ መምህራን በተገቢው መንገድ መቼ እንዴትና ምን ወይም የትኛውን ቁሳቁስ ለየትኛው ትምህርት ተገቢ ነው የሚለውን ማወቅ አለባቸው፡፡ Sells (1981፡263) ትክክለኛ የሆነ የማስተማሪያ ቁሳቁስ በትክክለኛው ጊዜና ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

### 2.1.6.5. ምዘና

በመማር ማስተማር ሂደት በትምህርት ዕቅዳቸው መሠረት ለተማሪዎቻቸው የቀረቡትን የትምህርት ይዘት ተማሪዎች መረዳትና አለመረዳታቸውን የተነደፉት ዓላማዎች ከግብ መድረስ አለመድረሳቸውን በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው፡፡

Dorothy (1985፡32) “ብቁ መምህራን ያለማቋረጥ ያስተማራቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩ ባዘጋጁት መሥፈርት ይመዝናሉ፡፡ መምህሩም ራሱን ይመዝናል፡፡ ይኸውም የተማሪዎችን ፍላጎት መጠበቅ አለመጠበቁን የተጠቀሙባቸው የትምህርት ማጠናከሪያዎች ተገቢ መሆናቸውን በተማሪዎቹ መካከል ባለው ልዩነት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠና በራሱና በተማሪዎቹ መካከል የነበረውን መስተጋብር በቂ መሆን አለመሆኑን ራሱን

ይጠይቃል" በማለት ይገልጻሉ፡፡ይህ ማለት ለመማር ማስተማር ሂደት በነደፈው የትምህርት ዕቅድ መሠረት የታለመው የትምህርት ዓላማ በትምህርቱ ሂደት ለተማሪው መድረሱንና አለመደረሱን ማወቂያው መንገድ የተለያዩ የመመዘኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ መልመጃዎችን በማሠራት፣ በተለያዩ ጊዜያት የሙከራ ፈተናዎችን በመስጠት ተማሪዎቹ ምን ያል የባህርይ ለውጥ እንዳመጡ ለመገምገም የሚረዳው ስልት ነው፡፡

ይህ ክፍል ተማሪዎች የተማሩትን ወደ ተግባር እንዲያሸጋግሩ የሚደረግበትና በዚህም ጥረት ውስጥ ብቃታቸዉ የሚፈተሽበት ክፍል ነው፡፡ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ውስጥም መምህሩ ተማሪዎቹን እንዴት ወደ ትግበራ መምራት እንደሚችል በግልፅ ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር htt;/www.crit.umich.edu/gsis/Pg-1.php በተዘጋጀዉ ዕለታዊ እቅድ ውስጥ ግምገማ ማድረግ ተማሪዎቹ የሚያሳዩት የግብረገብ እንቅስቃሴ የማስገንዘብ ብቃት ይኖረዋል በማለት ይገልጻል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው መሠረት ያስተማሩትን በመመዘን የሚያዘጋጁት መመዘኛች ለተማሪዎቹ ሲቀርቡ ምን ዓይነት ሥርዓት መከተል እንደሚገባቸው Ray (1969፡26) ሲገልፁ፡- መመዘኛቹ ግልጽና የተመጣጠኑ መሆን አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰሩትን ጠንቅቀው እንዲያውቁ መመሪያዎችን በግልፅ ማሳወቅ ለምን እና እንዴት እንደሚሰሩ ተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን ሰርተው ካበቁ በኃላ በሥራቸው ላይ ለመወያየት ክፍለ ጊዜ መወሰን በመጨረሻም ከመካከላቸው ለሚፈጠረው ልዩነት የሚረዳ ውጤት መስጠትም የተገባ ነው ይላሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እንኳን በቀላሉ ተረድተው ለውጤታማነት ራሳቸውን ሊያዘጋጁ ይችላሉ ለማለት የቀረበ ሃሳብ ይመስላል፡፡

### 2.1.7. የቋንቋ ትምህርት አተገባበር

የቋንቋ ትምህርት አተገባበር ማለት በትምህርት ዕቅድ ተነድፎ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የተማሪው የቋንቋ ብቃት መለኪያ ወይም መመዘኛ ስራ ላይ የሚውልበት መንገድ ነው፡፡ የትምህርት ዕቅድና የትምህርት ዕቅድ አተገባበር ሁለቱ ግንኙነት አላቸው የትምህርት ዓላማ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የትምህርት ዕቅድና ማስተማርን አቀናጅቶ ማሰናዳት ይገባዋል፡፡

አንድ የቋንቋ መምህር የትምህርት ዕቅድ የማይጠቀም ከሆነ ምን እና ማንን እንደሚያስተምር ትምህርቱን ከምን ላይ እንደሚጀምረውና ፍፃሜው ምን ላይ መሆን እንዳለበት ማወቅ ሊሳነው ይችላል፡፡ Dorothy (1985፡48) ለማንኛውም የትምህርት ሂደት የሰመረ ውጤት እንዲኖረው መሠረቱ በትምህርት ሂደት ላይ መፈፀም የሚገባውን አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡ ይህም የተማሪዎችን ልምድና የባለፈውን ትምህርት ከትምህርት ዕቅድ ውስጥ ካላካተተ የትምህርት ዕቅዱን አተገባበር ይቀንሰዋል ለማለት ይመስላል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ የሚፈለገውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የባለፈውን የአሁኑንና እንዲሁም የወደፊቱን የትምህርት አሰጣጥ ለመወሰን አጋዥነት አለው፡፡ Dorothy (1985፡46) “የትምህርት ዕቅድ አተገባበር ለቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ትምህርቶች ጭምር ነው፡፡ የተሳካ ዕቅድ ለመምህሩ ስለ ትምህርቱ ዓላማ፣ ስለ ተማሪዎቹ ፍላጎት ዝግጅት እንዲሁም የተማሪዎቹን ምርጫ በግልፅ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ያደርገዋል፡፡ የቋንቋ ዕቅድ መምህሩ ምን ማስተማር እንዳለበት ብቻ ሣይሆን ያዘጋጀውን ትምህርት እንዴት ማቀናጀትና መተግበር እንዳለበት ይመራዋል” በማለት ይገልጻሉ፡፡

ይህ የምሁሩ ሀሳብ የሚያሳየው በትምህርት ዕቅድ የማይጠቀም አንድ መምህር አንድን ቁምነገር ለማስጨበጥ ብዙ ጊዜ ያባክናል፡፡ የማስተማር ዕቅድ የሚያውቅ ሌላ መምህር ያንኑ ትምህርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያስተምር ይችላል፡፡ ስለዚህ የትምህርት ዕቅድ ጊዜንና ጉልበትንም ለመቆጠብ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም አንድ ትጉ መምህር በተፈለገው ጊዜና ወቅት ተገቢውን ዕውቀት ለተማሪዎች ለማስጨበጥ ተደጋጋሚና አሰልቺ ትምህርት እንዳይሰጥ ሁል ጊዜ በአዲስ መንፈስ አዲስ ነገር ለተማሪዎቹ እንዲያቀርብ ይረዳዋል፡፡ እንዲሁም የሰራውንና ያልሰራውን ለመለየት ይረዳዋል፡፡

### 2.1.8. ጥራት ያለውን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ዋና ዋና ነጥቦች

ጥራት ያለውን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት መከተል የሚገባን አሥር ዋና ዋና ነጥቦች htt;//American .org.state.gov/tiled/ae/resource በሚከተለው መልኩ ገልጾታል፡፡

1. ምን ለማስተማር ትፈልጋለህ ይህ የሚወሰነው የክፍል ደረጃ መለየት ነዉ፡፡ የትምህርት ቤት ደረጃም /standared/ መገለፅ አለበት፡፡

2. ለማስተማር ያቀድከው በትክክል በዕቅዱ መስፈሩ ግልፅና ውስን አላማ መያዙን ማረጋገጥ ፣

ለምሣሌ፡- የቃል ክፍሎችን ብንወስድና በአግባቡ አላማውን ማስቀመጥ መስተዋድድ፣ ግስ፣ ቅፅል…

3. አላማውን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የምንጠቀምበት መረጃ መሣሪያ በትምህርት ዕቅድ ውስጥ መገለፅ አለበት፡፡
4. የተማሪውን የመማር ፍላጎት ለመጨመር በተለያዩ መንገድ ትምህርቱን ማቅረብና ለአላማው ግልፅነት ማቀድ
5. በጭውውት ቀርበው ከሆነ ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተማሪው እንዲሣተፍ ማድረግ
6. ከርዕሱ ጋር ተቀረራቢነት ያላቸውን ጉዳዮች ተማሪው እንዲያቀርብ መወሰን
7. ርዕሱ ውስጥ ካሉት ጥያቄዎች የተወሰኑትን ማቅረብ ይህም በቀጥታ ከአላማ ጋር ይገናኛል፡፡
8. ጥቂቶች የትምህርት ዕቅዳቸውን ባይገመግሙም በአብዛኛው ጋር ማገናኘታቸውን ይገመግማሉ፡፡
9. የሚዘጋጅ ጥያቄዎች (መልመጃዎች ) ተማሪን ለማሳተፍ ብዙ እገዛ ያደርጋሉ፡፡
10. የሚዘጋጀዉ ዕቅድ በአንድ አሊያም በሁለት መልኩ ከሌላ ትምህርት ጋር ይገናኛሉ፡፡ ምሳሌ ሁለት ብርቱካን ሶስት ብርቱካን በመልክ ቢለዩና በጣዕም ቢጠየቁ ሂሣብና፣ ሳይንስን በቋንቋ ገልፀናል ማለት ነው፡፡

### 2.1.9. የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

የትምህርት ዕቅድ መርህ ሐሰቦችን አጠናክሮ በቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገገጃጀት ላይ በትክክል ለማስፈር ተፅእኖ ያመጣሉ የሚሏቸውን Musica (1991፡421-422) እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል፡፡ በትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ላይ በመሠረታዊነት ደረጃ ተፅእኖ ሊያመጡ ከሚችሉት ጉዳዮች አንዱ ጊዜ ነው፡፡ ይህም የመንፈቀ ዓመቱን ሁኔታ፣ ማለትም የክፍል ጊዜውን ድግግሞሽ እና እርዝማኔ የተመለከተ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው የተማሪዎች የዕውቀት ደረጃ ተመጣጣኝ መሆኑንና አለመሆኑን ይመለከታል፡፡ ይህም በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የዕውቀት ወይም የችሎታ ልዩነት መጠኑ ምን ያህል ነው የሚለውን ይመለከታል፡፡ ሌላው የተማሪዎቹ ልዩነት በዕድሜ ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ለትምህርት ባላቸው ፍላጎት እና የተማሪዎችን ግላዊ ሁኔታ

ይጨምራል፡፡ በመጨረሻም ስለትምህርቱ ቀደም ሲል ያላቸውን እውቀትና ግንዛቤ በዕቅዱ አዘጋጃጀት መርህ ግብር ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

Musica (1991፡450) እንደሚሉት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ትምህርቱን በጥራት ለመስጠት የተማሪው መጠን ፣ የክፍሉ ሁኔታ፣ የተማሪው አቀማመጥ ፣ የክፍሉ የብርሃን ድምቀት እና የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም የመርጃ መሣሪያዎች በዚሁ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ይላሉ፡፡ እነዚህ መርህ ሀሳቦች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ቢዘጋጅ አመርቂ የሆነ የትምህርት ውጤት ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ የዓመቱ የትምህርት ጊዜ እንዲሰምርና በተማሪዎች ላይ የአሠራርና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲታዩ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል፡፡ በማለት አካባቢያዊ ዳራ በሚዘጋጀው የትምህርት ዕቅድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ጽንሰ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

### 2.1.10. የትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚያጋጥሙ ስህተቶች

Bob Kizlik የተባሉት እንደጠቀሱት "የትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ በተለያዩ ምክንቶች ስህተት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እነዚህንም ከአሁን በፊት እንዳየሁት እና በመቶ የሚቆጠር የትምህርት ዕቅድ ስገመግም አያሌ ስህተቶች አግኝቼባቸዋለሁ፡፡" ይላሉ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. የትምህርት እቅድ በግልፅ አልሰፈረም፣
2. የትምህርት እቅድ በአግባቡ ተወስኖ አልታየም፣
3. በትምህርት አላማ ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት ውስጥ 70% ውን አያሳይም፣
4. የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ከትምህርት ዕቅድ ጋር አይዛመድም፣
5. ለተማሪው የሚተላለፈው መልዕክት ግልፅ አይደለም፣
6. የተማሪው ተሣትፎ በቀጥታ ከዕቅድ ጋር የሚገናኝ አላማ የለውም፡፡ አንድ ዕቅድ ከነዚህ ከተጠቀሱት ውስጥ የአንዱ ተጠቂ ነው፡፡

http//www.adprima.com/mistaks.htm ይህ የሚያስረዳው የትምህርት ዕቅድ በሚነደፍበት ወቅት ግልፅመሆን እንዳለበት፤ ውስን እና ሊተገበር የሚችል አላማ ብቻ ሊኖረው

እንደሚገባ፣ በዕቅዱ ውስጥ የሚካተቱት የትምህርት ዕቅድ አካላት ተጣጥሞሽ ሊኖራቸው እንደሚባ የሚያሳስቡ ናቸው፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን አስመልክቶ ጥናት እየተደረገ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ጠንካራ የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ስልቶች የሚቀጥሉበትን ደካማ የማስተማሪያ ስልቶች ደግሞ የሚሻሻሉበትን መፍትሔ መፈለግ ተገቢ ነው፡፡

በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን አስመልክተው የተጠኑ ስራዎችን ለማየት ጥረት ተደርጎዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች በሚፈለገው መጠንና ደረጃ ማግኘት ባይቻልም መጠነኛ ተዛማጅነት ያለውን ማግኘት ተችሏል፡፡ይኼውም ኮከቤ መኮንን (2002) ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ሲባል በቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር  ላይ ጥናታቸውን በማካሄዳቸው ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

ኮከቤ መኮንን (2002) "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በወንምበራ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች" በሚል ርእስ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር መምህራን ምን እንደሚመስል በመፈተሽና የሚታዩ ችግሮችንም ለይቶ የመፈትሔ ሃሳብ ለመጠቆም ዓላማ በማድረግ ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ላይ በመነሳትም የደረሱበት ውጤት መምህራን በትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ መሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም ትምህርቱ ዓላማ ፣ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ፣ የመምህሩ ሚና ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ተካተውና ተሟልተው አለመታቀዳቸውን በጥናቷ ደርሳበታለች፡፡ ከዚህ በመንሳትም ከላይ እንደ ችግር ያነሳቻቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ተገቢውን መስፈርት ያሟላ ዕቅድ ማቀድ አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ጥናታቸውን አጠናቀዋል፡፡

ከላይ የተገለጹት ጥናት አቅራቢ ያላዩት እና የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው የሚከተለው ነው ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ

የሚታየውን የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍ ከተሰጠው የትምህርት ጊዜ ጋር አጣጥመው አለማጠናቀቅ እና የሚዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ እቅድ ከተሰጠው ጊዜና ሰዓት ጋር ተጣጥሞ ያለመዘጋጀት ችግር በመለየት ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ለትምህርት የተሰጠው የማስተማሪያ ጊዜ ሰሌዳ ከተዘጋጀው የትምህርት  እቅድ ጋር ያለመመጣጠን ወይም ሌሎች ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ጥያቄ  ያሳደረበት በመሆኑ ከዚሁም ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ችግሮች ነቅሶ በማውጣትና በማሳየት ጥናቱን አካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት የሚያደርገው የአጠናን ዓይነት ገላጭ የጥናትና የምርምር ስልት ነው፡፡ ይህ ጥናት የተመረጠበት ምክንያት በጢሮ አፈታ ወረዳ በሚገኙ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ቤት፤ አኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የሚገኙ መምህራን የሚያዘጋጁቸውን የአማርኛ ቋንቋ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ያሉባቸውን ችግር ምን እንደሚመስል ለማሳየት እና የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህን ጥናት ለማካሄድ ተስማሚ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው የምርምር አይነት ገላጭ የምርምር ዘዴ ነው፡፡

በመሆኑም አጥኚው ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ደግሞ አይነታዊ የምርምር አይነትን ተጠቅሟል፡፡

### 3.2. የተጠኝ ናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ዓላማ ተግባራዊነት በይሁነኝ ናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጡት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጢሮ አፈታ ወረዳ በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ቤት፤ አኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) እና በኦሞናዳ ወረዳ ውስጥ በተመረጡ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ኦሞ ናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ናቸው፡፡ አነዚህ ትምህርት ቤቶችም በይሁነኝ ንሞና የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው ፡፡

#### 3.2.2. የክፍል ንሞና አመራረጥ

በአምስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉት የአስረኛ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ሃያ አምስት ናቸው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናታዊ ስራ የተመራጡት የመማሪያ ክፍሎች አስር ናቸው፡፡ ክፍሎች በናዳ ሁለተኛ ደረጃ ካሉት አራት የ10ኛ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ

10ኛA እና 10ኛD፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ካሉት ስድስት የ10ኛ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ 10ኛA እና 10ኛD፣ በዲምቱ ካሉት ስድስት የ10ኛ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ 10ኛC እና10ኛF፣ በአኮ ሁለተኛ ደረጃ ካሉት አምስት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ 10ኛA እና 10ኛF በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ካሉት አራት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ 10ኛA እና 10ኛB በአጠቃላይ አስር የመማሪያ ክፍሎች በእጣ ንሞና ዘዴ ተወስደዋል፡፡

### 3.2.3. የመምህራን አመራረጥ

በአምስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት አስር ናቸው፡፡ በመሆኑም አጥኚው የመረጠው የናሙና አይነት ወሳኝ ንሞና (Non probability Sampling) ስር የሚገኘውን አመቺ ወይም የግኝት ንሞና (Convenience Sampling) ነው፡፡

በመሆኑም አጥኚው ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀሙ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል፡፡ ምክንያቱም ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን አስር ብቻ መሆናቸው ለምርምሩ አስፈላጊና በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ ስለወሰነ ወይም ለምርጫ ዕድል ስለሌለው መረጃ ሊያገኝ የሚችልባቸው ሰዎች በጣም ውስን ስለሆኑ፤ንሞና መምረጥ አስፈላጊ ስላልሆነና ባገኛቸው ሰዎች መረጃ መሰብሰብ ግድ ስለሆነ ነው፡፡

### 3.2..4. ሣምንታዊ ትምህርት ዕቅድ ናሙና አመራረጥ

ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት እቅድ አላቸው፡፡ የመምህራኑን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በናሙናነት መርጦ የሚጠቀምበት ምክንያት በአምስቱም ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ የቋንቋ መምህራን እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ከአምስቱም ትምህርት ቤቶች ካሉ መምህራን በመጋቢትና ሚያዚያ ወር ከታቀዱት ሳምንታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ ከእያንዳንዳቸው መምህራን ሶስት ሶስት በድምሩ 30 እቅድ በመውሰድ መረጃው ተተንትኗል፡፡ አጥኚው በነዚህ ወራት የታቀዱትን እቅዶች የመረጡበት ምክንያት ከያዘው የጥናት ፕሮግራም ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ነው፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በጥናታዊ ፅሁፍ አዘገጃጀት ወቅት በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቢኖሩም ለዚሁ ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው የተጠቀመበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚከተለው ነው፡፡

#### 3.3.1. የመዛግብት ፍተሻ

በአምስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመጋቢትና በሚያዚያ ወር ያዘጋጇቸውን የ10ኛ ክፍል እቅዶች ከአስሩም መምህራን አምስት አምስት እቅዶችን በመመርመር ስለ ሳምንታዊ/ ዕለታዊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር መረጃ ሰብስቧል፤ እንዲሁም የተሰበሰበውን መረጃ በአግባቡ በማደራጀትና በመተንተን የተገኘውን ውጤት አስቀምጧል፡፡

#### 3.3.2. ምልከታ

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ከተሰጠው የትምህርት አላማ ይዘት የትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ለማየት ምልከታ ተደርጓል፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የመማር ማስተማር ሂደት ምን እንደሚመስል በተጨባጭ የሚያሳየን የመረጃ መሰብሰቢያ ሥልት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የክፍል ውስጥ ምልከታ አጥኚው ተጠኚዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባርና ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በአይኑ እንዲያይ በጆሮው እንዲሰማ ከሚያደርጉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ያለው (2006፡188)

*"የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅጽበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡ እንደ ቃለ መጠይቅ ወይም እንደ ጽሑፍ መጠይቅ ለመላሹ ጥያቄ ቀርቦለት መላሹ ከራሱ የሚመልሰው ሳይሆን ተመራማሪው ተጠኚዎቹ (እያወቁም ሆነ ሳያውቁ) በሚገኙበት ቦታ በመሆን በዚያ ወቅት ምን እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚሰሩ፣ እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚራከቡ፣ ምን እንደሚናገሩ፣...ወዘተ እራሱን በሚመቸው፣ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ በሚያስገኝለት መንገድ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡"* በማለት ያለውን ሀሳብ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ

በመነሳት መረጃዎችን በቦታቸው በመገኘት መመልከት፣ መስማትና መመዝገብ ቀጥተኛ የሆነ መረጃ ማግኘት ስለሚያስችል የክፍል ውስጥ ምልከታ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም አጥኚው 'ቼክ ሊስት' በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዴት እየተካሄደ እንዳለ እና የክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በመመልከት መረጃ መሰብሰብ ስላለበት ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ከናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣በጢሮ አፈታ ወረዳ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም ከዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣ ከአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት ፣ ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት ክፍሎችን በድምሩ አስር 10ኛ ክፍሎችን በእጣ ንሞና በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታ አካሂዷል፡፡ በተመረጡት የ10ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎችም ለሶስት ሶስት ዙር በባለ ሁለት ድርድር (አዎ አይደለም) መልክ የተዘጋጁ አስራ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ምልከታ አካሂዷል፡፡ ለክፍል ውስጥ ምልከታ የተዘጋጁ የማረጋገጫ ዝርዝሮችም (ቼክ ሊሰት) በሶስት ክፍል የተመደቡ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹም የሚያጠነጥኑት የዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክቶ፣ የዕቅድ  አተገባበርን አስመልክቶ እና የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን አስመልክቶ የአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን ለመፈተሽ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ምልከታ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የእያንዳንዱን ጥያቄ ውጤት ከማስቀመጥ ይልቅ በሶስት ክፍል በመመደብ በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ትንንታኔ ተሰጥቷል፡፡

### 3.3.3. ቃለ መጠይቅ

ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በፅሁፍ የተዘጋጀ መጠይቅ ቀርቧል፡፡  አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከመጠይቁ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውና ከተሰጠው ምላሽ ጋር በተያያዘ ለዚህ ጥናት ይጠቅማል ተብሎ የታሰብ የተለየ ሀሳብ በተያያዥነት ቀርቧል፡፡ ቃለ መጠይቅ በፅሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ አናገኛቸውም ብለን የምናስባቸውን መረጃዎች ለማግኘት የሚጠቅም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡

አለም እሸቱ (1997፡65) እነ veit (1990) ጠቅሶ እንደገለጸው ቃለ መጠይቅ መረጃን ከዋናው ከምንጩ የመሰብሰቢያ አንዱ መንገድ በመሆኑም ርቱእ የመረጃ ምንጮችን በመመርኮዝ የተሻለና የበለጠ አስተማማኝነት ያለው መረጃን ሰብስቦ ለማጠናቀር ያስችላል በማለት ያስረዳል፡፡ ይህ የሚያስረዳው የመረጃ ምንጭነቱ ተጨባጭና ተአማኒነቱ የጎላ መሆኑን የሚገልጽ ይመስላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ያለው (2006፡182) እንደገለፀው ከሆነ ቃለ መጠይቅ ለመላሹ ጥያቄዎችን ለማብራራት፣ ግልጽ ያልሆኑ ምላሾችን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ መላሹ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድና የተፈለገውን መረጃ እንዲሰጥ ለማድረግ ስለሚያስችል ጠንካራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ይሰኛል በማለት አስቀምጧል፡፡

በመሆኑም ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ሰፋ ያለና የተብራራ ሀሳብ ለማግኘት የሚያስችልና አጥኚው ተጠኚውን ወደ ተፈለገው አቅጣጫ በመምራት ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ስለሚችል የጥናቱን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይችላል ከሚል አንፃር ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመጠቀም ችሏል፡፡

ቃለ መጠይቁ በሚካሄድበት ሰዓት ለተጠያቂዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች አስቀድመው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አጥኚው መረጃ አገኛለሁ ብሎ ያሰባቸውን ጥያቄዎች በየመሀሉ እያፈለቀ ተጠያቂዎቹ በነፃነት እንዲመልሱ የሚገፋፉ ጥያቄዎችን በመጠየቁ ውስን ቃለ መጠይቅና ነፃ ቃለ መጠይቅ መጠቀሙ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ቃለ መጠይቁም የተካሄደው መምህራኑን በአካል በመገናኘትና በማነጋገር ለነሱ አመቺ የሆነ ጊዜ በመምረጥና ቀጠሮ በመያዝ ተከናውኗል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ ከሚያካትታቸው ተጠኝዎች አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ የቃል መጠይቆች ተደራጅተው ተቀምጠዋል፡፡ በመጠይቁና በክፍሉ ውስጥ ምልከታ አማካኝነትም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ግልፅና ተገቢነት ያላቸው ገላጭ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡

እነዚህ መረጃዎችም በአግባቡ ከተደራጁ በኃላ ለእያንዳንዳቸው መጠይቆች አስፈላጊው ትንተና በበቂ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ለመጠይቆቹ የተሰጡት ምላሾችና የተሰበሰበውን መረጃ

የተተነተነውና የተብራራው የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በአይነታናዊ ምርምር የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማደራጀትና በማብራራት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ የተገኘውን መረጃ እውነተኛነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል የቃል መጠይቁንና ጥያቄዎችና ለክፍል ምልከታ የቀረቡትን መገምገሚያ መስፈርቶች ለአማካሪ በማሳየትና በማስገምገም ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በመረጃ መተንተኛ ሂደት ውስጥ አጥኚው ለጥናቱ አመቺ የሆነውን አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

በዝግ እና በነጻ ጥያቄዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃዎች እና በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በአጠቃላይ አጥኚው በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃል መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ የሰበሰባቸውን መረጃዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምእራፍ አራት

## የመረጃ አቀራረብና ትንተና

ይህ ምእራፍ በሰነድ ፍተሻ፣ በክፍል ውስጥ ምልከታ እና በቃል መጠይቅ  የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚተነተኑበት ክፍል ነው፡፡ ምእራፉ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል በናሙናነት ስለ ተመረጡት ተጠኚዎች ግላዊ መረጃ የያዘ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የዋናውን ጥናት ትንታኔና ገለፃ የሚመለከት ክፍል ነው፡፡

### 4.1 የተጠኝዎች ግላዊ መረጃ

በዚህ ንኡስ ክፍል በናሙናነት ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ መምህራን ግላዊ መረጃ የሚቀርብበት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ተተኳሪ ያደረጋቸው 10 መምህራንን ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ መረጃ ሰብሳቢው ባደረገው የቅርብ ክትትል 10 መምህራን ያለ አንዳች ችግር መረጃ ለመስጠት ችለዋል፡፡ በመሆኑም መረጃውን በሚገባ ያጠናቀቁ እና የመለሱ ተጠኚዎች ግላዊ መረጃ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መጠይቁን በመመለስ የተሳተፉ መምህራን ጾታ ፣ የትምህርት ደረጃና የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቶች ስም | የመምህራን ብዛት | | | የትምህርት ደረጃ | | | የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ዲፕሎማ | ዲግሪ | ድምር | አቢ.ይ | ንዑስ |
| 1. | ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ | 1 | - | 1 | - | 1 | 1 | አማርኛ | English |
| | | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 | አማርኛ | አፋንኦሮሞ |
| 2. | ገበሬ ሁለተኛ ደረጃ | 2 | - | 2 | - | 2 | 2 | English | አማርኛ |
| 3. | አኮ ሁለተኛ ደረጃ | - | 1 | 1 | - | 1 | 1 | አማርኛ | - |
| | | 1 | - | 1 | - | 1 | 1 | English | አማርኛ |
| 4. | ናዳ ሁለተኛ ደረጃ | 1 | 1 | 2 | - | 2 | 2 | አማርኛ | English |
| 5. | አሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ | 1 | 1 | 2 | - | 2 | 2 | አማርኛ | English |
| | ድምር | 6 | 4 | 10 | - | 10 | 10 | - | - |

ከላይ በተገለፀው ሠንጠረዥ ውስጥ ያለው በትምህርት ቤቶቹ ያሉት መምህራን የተለያየ ዳራ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት መምህራን ብዛት 10 ሲሆን በፆታቸው 6 ወንዶች እና 4 ሴቶች ናቸው፡፡ ከትምህርት ደረጃቸው አንፃር ስናይ ደግሞ ሁሉም በተመሳሳይ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ከሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ስናያቸው ሰባት መምህራን አማርኛን አቢይ፣ ከነዚህ ውስጥ አምስቱ እንግሊዝኛን ንዑስ አድርገው የተማሩ ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ መምህራን ግን አንዱ አፋን ኦሮሞን በንዑስነት ሲወስዱ ሌላኛዋ ደግሞ በንኡስነት የወሰዱት የትምህርት አይነት እንደሌለ ያሳየናል፡፡ ሌሎቹ ሶስት መምህራን እንግሊዝኛን አቢይና አማርኛን ንዑስ አድርገው የተማሩ መሆናቸውን ያስረዳናል፡፡ ይህም ለጥናቱ አጥጋቢ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

## 4.2. መረጃ ትንተና እና ገለጻ

በዚህ ንኡስ ክፍል ስር ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ፣ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ እና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናት በሰነድ ፍተሻነት ተተኳሪ የሆነው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያዘጋጁአቸው የዕለታዊ ዕቅድ ይሆናል፡፡ ይህም የቋንቋ ትምህርት ሲዘጋጅ ከአላማ አንጻር እንዴት ይነደፋል ይዘቱስ ምን መምሰል አለበት የሚሉትን እና አንድ የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ ምን ምን ይዘቶችን ማካተት አለበት የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በቅደም ተከተል ተተንትኗል፡፡

አጠቃላይ የመምህራኑ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በተመለከተ ከትምህርት ቤቶቹ የቋንቋ መምህራን የተገኘ የቃለ መጠይቅ ምላሽ በቅደም ተከተል ተተንትኗል፡፡ መምህራኑ በየትምህርት ቤቶቹ የሚዘጋጁቸው የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ዕቅድ ከአላማ አንጻር እንዴት ተዘጋጅቷል የሚለውን ለመቃኘትም ተሞክሯል፡፡ የትምህርት ዕቅዱ አላማ Bloom's Taxonomy **kirkpatrick's learning model**ን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

እንዲሁም የትምህርት ዕቅድ ይዘትን በተመለከተ ደግሞ The Modeline Hunter lesson Design modelን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በተመለከተ ተመራማሪዎች ያስቀመጡትን መስፈርት በመዳሰስ

ተገቢ የሆነ ትንታኔ ለመስጠትም ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት የትምህርት ዕቅድ አላማ ሲነደፍ መታወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ተተንትኗል፡፡

አንድ መምህር ለማስተማር ወደ ክፍል ከመግባቱ በፊት በየዕለቱ ማስተማር የሚገባውን ትምህርት በተመለከተ አስቀድሞ ዓላማ መንደፍ አለበት፡፡ ለተማሪው በዕለቱ ማቅረብ የሚገባውን ትምህርትና የሚጠበቅበትን የባህሪይ እና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በተገቢው ሁኔታ መነደፍ አለባቸው፡፡ አነዳደፋቸውን በተመለከተ Elizzabeth (1982፣13) ሲያሰረዱ የመማር ማስተማር ዓላማዎች መገለፅ ያለባቸው ተማሪዎች በወቅቱ የተመደበላቸውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣ የተማሩትን እንዴት መተግበር አለባቸው ከሚለው አንፃር መሆን አለበት፡፡ የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ስንነድፍ ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ ተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ ማስቀመጥ እንጂ መምህሩ ምን ማድረግ እንዳለበት ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡

የትምህርት ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በግልፅ መስፈር አለባቸው፡፡ Dorothy (1985፣45) ሲያስረዱ "ዓላማዎች መገለጽ ወይም መነደፍ ያለባቸው ሊስተዋልና ሊለካ ወይም ሊገመት በሚችል መንገድ መሆን አለበት" ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በማያይዝ Ray (1969፣19) የመማር ማስተማር ዓላማ በግልፅ መስፈር እንዳለባቸው ሲያብሪሩ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ የሚፃፉ ዓላማዎች ውስንና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ ወይም የተማሪዎችን የባህሪይ ደረጃ የሚገመግምና የሚያስፈልገውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሆን አለባቸው ይላሉ፡፡ Ray (1969፡24) መምህሩ በሚያዘጋጀው የዕለት ተዕለት የትምህርት ዕቅድ አነዳደፍ የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስ እንዲችል ሆኖ ቢዘጋጅ ተመራጭነት ይኖረዋል ይላሉ፡፡

1. ዓላማዎቹ በክፍል ውስጥ የተማሪውን ፍላጎት ችሎታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ

ናቸውን ?

2. ዓላማዎቹ የተወሰኑ ናቸውን ከሚፈለጉት ባህሪያት ፣ ከተጠቃሚ ዕሴቶች ወይም ጉዳዮች ጋር ዝምድና አላቸውን?

3. ዓላማዎቹ በሐሳብ ፣ በምልክት፣ በእሴት ፣በልምድ ወይም በስሜት እንዲገለፁ ሆነዋል?

4. ለስኬማነታቸው ለተማሪው የባህርይ ብቃት በማሰገኘት በጎ/ አበረታች/ የባህሪይ ለውጥ በማምጣት ይረዱታልን?

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ የሆኑ የቋንቋ ትምህርት አላማዎች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በትምህርት ቤቶቹ የተከናወነውን የዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ለመዳሰስ የተከናወነው የክፍል ውስጥ ምልከታ ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

### 4.2.1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ ሰነድ ፍተሻ ትንተና

በሁሉም ትምህርት ቤቶች በተደረገው የሰነድ ፍተሻ የትምህርት ቤቶቹ ዕቅዶች በአላማ ስር ያስቀመጡትን በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በአላማ ስር የተቀመጡትን ዕቅዶች ደግሞ Benjamin በሶስት ቦታ ከፋፍሎ ባስቀመጧቸው የግንዛቤ መስፈርቶች ማለትም (Cognitive (አእምሮታዊ), Affective(ስሜታዊ) እና psychomotor (ከላይ አካላዊ) ተብለው ተከፋፍለው ተቀምጠዋል፡፡ አላማዎቹን በየምድባቸው ከፋፍሎ ለማየትና በቀላሉ ለመረዳት እንዲቻል የተነደፉትን የትምህርት ዕቅድ አላማዎች በዝርዝር ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ተማሪዎቹ ይህንን ትምህርት ተምረው ሲያጠናቅቁ ፡-

- ተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ያዉቃሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ዘገባ አፃፃፍ ይገነዘባሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቀረበዉን ምንባብ ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቃላት ችሎታቸዉን ያጎለብታሉ፡፡
- የቤተ መጻህፍት አጠቃቀምን ያውቃሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይረዳሉ፡፡
- የቃለ ጉባኤ አያያዝን ያውቃሉ፡፡
- እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺዎችን ይናገራሉ፡፡
- ቅድመ ድርሰት ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡
- የድርሰት መሰረታዊ ነገሮችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ከነፍቺያቸው ይገልጻሉ፡፡

- የግጥም አይነቶችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ምዕላድን ነፃና ጥገኛ ብለው ይከፋፍላሉ፡፡
- አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ተጠቅመው ስዕላዊ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- በተለያየ የዓረፍተ ነገር ስልቶች ዓረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ህብረ ቃላቸውን በመለየት ቅኔዎችን ይፈታሉ፡፡
- የዓረፍተ ነገር አይነቶችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገር እየገነቡ ያሳያሉ፡፡
- የቅኔን ህብረ ቃል በማውጣት ሰምና ወርቅን ይለያሉ፡፡
- ህብረ ቃል ከለዩ በኋላ በፍቺዎቻቸው ልዩ ልዩ ቃላትን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የልቦለድና የኢልቦለድ አንድነትንና ልዩነትን ይገልጻሉ፡፡
- ከግስ ስምንና ቅጽልን ይመሰርታሉ፡፡
- ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ያሟላሉ፡፡
- ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የንግድ ስራ ደብዳቤን እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡
- ምንባቡን በትክክል ያነባሉ ፤ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- ድርብና ነጠላ ትዕምርተ-ጥቅሶችን በተገቢው ቦታ ይጠቀማሉ፡፡
- የግጥማዊ ስነ-ቃሎችን ሃሳብ ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- መመሪያን ተከትለው ይወያያሉ፤ ይከራከራሉ፡፡ የሚሉት ከመጋቢትና ሚያዚያ ወራት ከተሰበሰቡት የመምህራን ዕቅዶች ማግኘት ተችሏል፡፡

በዚህ መሰረት ለመረጃነት በተሰበሰቡት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች ውስጥ የሰፈሩትን የአላማ ማሰሪያ አንቀፆችን በሶስቱ የግንዛቤ መለኪያ ስር ተመድበው በሚከተለው መልኩ ተቀምጠዋል፡፡

1. Cognitive domain (አእምሮታዊ ዘዴ) የምንለው የማሰብ ችሎታ ማለትም ዕውቀትን እና ማሰብን ወይም መረዳትን አሊያም ተረድቶ ውስጣዊ ባህርይን የሚመለከት ወይም አእምሮታዊ /cognitive/ ተግባር ነው፡፡ ይህ አእምሮታዊ የግንዛቤ ክፍል ልዩ መገለጫው በሚደረገው ውስጣዊ አስተሳሰብ ወይም ዕውቀት ላይ ማነጣጠሩ ነው፡፡ እነዚህ አእምሮታዊ

ዘዴዎች የመማር ውጤት በቀላሉ ላይታይ ወይም ላይለካ ይችላል፡፡ በተለይም ከመረዳት፣ ከማድነቅ ከዝንባሌ ወዘተ ጋር የተያያዙ ጉዳዩችን በተጨባጭ መንገድ ለመለካት ያስቸግራል፡፡ በዚህ መሰረት በአእምሮታዊ ተፅዕኖ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ከተሰበሰበው ዕቅድ ሰባቱ ይገኙበታል፡፡ እነዚህም፡-

- ተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ያዉቃሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ዘገባ አፃፃፍ ይገነዘባሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቀረበውን ምንባብ ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቃላት ችሎታቸውን ያጎለብታሉ፡፡
- የቤተ መጻህፍት አጠቃቀምን ያውቃሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይረዳሉ፡፡
- የቃለ ጉባኤ አያያዝን ያውቃሉ፡፡

እነዚህ ያውቃሉ፣ይገነዘባሉ፣ይረዳሉ እና ያጎለብታሉ የሚሉት የተማሪዎቹን ውስጣዊ ግንዛቤያቸውን የሚገልጹና የሚያስረዱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

2. Affective domain (ስሜታዊ ዘዴ) ሌላኛው የትምህርት አላማ አይነት እንዲያከናውን የሚፈለገው ጉዳይ በተጨባጥ የሚታይና የሚለካ ሲሆን ወይም ሳይሆን ከመቻሉ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንዳንድ የትምህርት አላማዎች በቀላሉ በሥራ ሊተረጉሙና ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የተፃፈን አንድ አረፍተ ነገር ለተማሪው ሰጥቶ ይህን ወደ አማርኛ እንዲተረጉም ቢደረግ ፣ በተግባር ሊገለፅ ወይም ሊታይ የሚችል አላማ ነው፡፡ ይህ ውጫዊ ባህርይን የሚመለከት ያደረገውን በተጨባጭ ማወቅ ይችላል፡፡ ከተሰበሰበው ዕቅድ አምስቱ በዚህ የሚፈለገው ጉዳይ የሚታይና የሚለካ ሲሆን ወይም ሳይሆን ከመቻሉ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህንም ከዚህ በታች የተገለጹትን ማሳያዎች ማየት ይቻላል፡፡

- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ከነፍቺያቸው ይገልጻሉ፡፡
- ድርብና ነጠላ ትዕምርተ-ጥቅሶችን በተገቢው ቦታ ይጠቀማሉ፡፡
- ምንባቡን በትክክል ያነባሉ ፣ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- መመሪያን ተከትለው ይወያያሉ፣ ይከራከራሉ፡፡

3. psychomotor domain (ባህርያዊ ዘዴ) - አላማ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚያተኩርበት ጉዳይ ይኖረዋል፡፡ ለምሣሌ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪው አንድን አይነት ተግባር ሰርቶ እንዲያሳይ የሚፈልግ ከሆነ ባህሪያዊ አላማ ይነድፋል፡፡ የተሟሟተ የቃላት አገባብ ያለው አንቀፅ ሰጥቶ ጽፎ እንዲያስተካክል ማድረግ ለዚህ በአብነት ሊጠቀምስ ይችላል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ በቋንቋ ክሂሎች /ማዳመጥ፤ መናገር፤ መፃፍና ማንበብ / ላይ ያተኮረ እነዚህን በማዳበር ላይ ያተኮረ ክሂላዊ አላማ ይኖረዋል፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ ይናገራል ይፅፋል የሚሉት አይነት ማሰሪያ አንቀፆችን የሚጠቀሙ ሊሆን ይችላል፡፡

- እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺዎችን ይናገራሉ፡፡
- ቅድመ ድርሰት ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡
- የድርሰት መሰረታዊ ነገሮችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የግጥም አይነቶችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ምዕላድን ነፃና ጥገኛ ብለው ይከፋፍላሉ፡፡
- አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ተጠቅመው ስዕላዊ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- በተለያየ የዓረፍተ ነገር ስልቶች ዓረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ህብረ ቃላቸውን በመለየት ቅኔዎችን ይፈታሉ፡፡
- የዓረፍተ ነገር አይነቶችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገር እየገነቡ ያሳያሉ፡፡
- የቅኔን ህብረ ቃል በማውጣት ሰምና ወርቅን ይለያሉ፡፡
- ህብረ ቃል ከለዩ በኋላ በፍቺዎቻቸው ልዩ ልዩ ቃላትን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ከግስ ስምንና ቅጽልን ይመሰርታሉ፡፡
- ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ያሟላሉ፡፡
- ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የንግድ ስራ ደብዳቤን እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡
- የግጥማዊ ስነ-ቃሎችን ሃሳብ ለይተው ይናገራሉ፡፡

እነዚህ ከላይ ለማሳያነት የተዘረዘሩት የትምህርት ዕቅድ አላማዎች ከብዛታቸው አንፃር ሲታዩ አስራ ዘጠኝ ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የሚታቀዱት የትምህርቱ አላማዎች

አብዛኞዎቹ ባህርያዊ ዘዴን (psychomotor domain) ትኩረት አድርገው የሚነደፉ የትምህርት ዕቅድ አላማዎች መሆናቸውን ያሳየናል፡፡

እነዚህ ከላይ በዝርዝር የተገለጹት የትምህርት እቅድ አላማዎች አብዛኞዎቹ ከይዘታቸው አንጻር ሲታዩና በዕለታዊ ዕቅድ ስር መነደፍ ከሚገባቸው አግባብ ሲመዘኑ አብዛኞዎቹ የተሻሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በዕለታዊ ዕቅድ ስር ሊነደፉ ወይም ሊታቀዱ የሚገባቸው የዕቅድ ዓላማዎች ከጥቅል ይልቅ በዝርዝር መቀመጣቸው ተገቢ ስለሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያዎቹ ረድፍ የተገለጹት ሰባት አላማዎች ማለትም፡-

- ተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍን ያዉቃሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ዘገባ አፃፃፍ ይገነዘባሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቀረበዉን ምንባብ ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎቹ የቃላት ችሎታቸዉን ያጎለብታሉ፡፡
- የቤተ መጻህፍት አጠቃቀምን ያውቃሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይረዳሉ፡፡
- የቃለ ጉባኤ አያያዝን ያውቃሉ፡፡ በማለት የተነደፉት ዓላማዎች የተቀመጡት በጥቅል በመሆኑ አግባብነት የጎደለው ይመስላል፡፡

እነዚህ አላማዎች የተገለፁበት ሊለኩና ሊመዘኑ በማይችሉ ቃላት ነው፡፡ ያውቃሉ፤ ይገነዘባሉ፤ ይረዳሉ፤ ያጉለብታሉ፡፡ አላማዎቹ በድርጊት መገለፅ በሚችሉበት መንገድ መስፈር ይችሉ ዘንድ ያውቃሉ፤ ይገነዘባሉ፤ ይረዳሉ ያጉለብታሉ ወዘተ...የሚሉት ቃላት በሌሎች ሊተኩና ሊመዘኑ በሚችሉ ቃላት መተካት ይኖርባቸዋል፡፡

ምክንያቱም በዕለታዊ ዕቅድ ውስጥ በአላማ ስር የምንጠቀምባቸው ቃላት በጥቅል መቀመጣቸው በዕለቱ ሊተገበር የተፈለገውን የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ዝርዝር አላማ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ዓላማ ሀሳብን የሚገልጽ ስለሚሆን ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ የቤተ መጻህፍት አጠቃቀምን ይናገራሉ፤ የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይለያሉ ፤ የቃለ ጉባኤ አያያዝን ይናገራሉ፤ በሚሉትና መሰል የአገላለጽ ስልት ቢገልጹ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ የትምህርት ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በግልፅ መስፈር አለባቸው፡፡ ይህን በተመለከተ Dorothy (1985፡45) ሲያስረዱ ”ዓላማዎች መገለጽ ወይም

መነደፍ ያለባቸው ሊስተዋልና ሊለካ ወይም ሊገመት በሚችል መንገድ መሆን አለበት” ይላሉ፡፡

የትምህርት ዓላማዎች ሲበዙ ትክክለኛ አይሆኑም ስለዚህ የትምህርት ዓላማዎችን ጠበብ አድርጎ ሁለት ወይም ሦስት ቁልፍ ሃሳቦችን፣ ወይም ተማሪዎችህ እንዲማሩ የተፈለገውን ክህሎት ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ መምህራን ሁልጊዜ የትምህርት ዕቅዳቸውን በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተመርኩዘው ማቀድ እንደሚጠበቅባቸው ይስማማሉ፡፡ ከነደፉት የትምህርት ዓላማዎች መካከል ቅድሚያ የሚሰጡት የትምህርት ዓላማ በወቅቱ የትምህርት ዕቅዳቸውን በተፈለገው ዓይነት እንዲያቅዱትና እንዲወስኑ ይረዳቸዋል፡፡ ተጨማሪ ምሣሌዎችንና አማራጭ ሥራዎችን መጠቀሙ ሥራቸውን ተለዋዋጭ እንዲሆን ያግዛቸዋል፡፡ Strategies to Extend Student Thinking htt፡/www.crt.umich.edu/gsis/p4 4.php.

ከዚህ በተጨማሪ የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ይረዳሉ ፤ የሚለውና የቃለ ጉባኤ አያያዝን ያውቃሉ፤ የሚሉት ሁለቱ በአላማ ስር የተቀመጡት በአንድ ቀን ዕለታዊ ዕቅድ ስር የታቀዱ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ዕቅድን በአንድ ዕለት የተለያየ ይዘት ያላቸውን አላማዎች መንደፍ ተገቢ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ዕቅዱን ከጊዜ አንጻር ለማጠናቀቅ ከማስቻል በዘለለ የሚሰጠው ፋይዳ ብዙ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የሚታቀዱት ዕቅዶች ከቅደም ተከተል አንጻር ሲታይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ነገር ሊኖር እንደሚገባ የሚያሳይ ነው፡፡

በናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀን 15/07/2008 በ10 D ክፍል የተስተዋለው የምልከታ ክንውንም ይህን የሚያስረግጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዕለቱ የቀረበው የዕቅድ ተግባርም የሚከተለው ነበር፡፡ መምህሩ “የአጭር ልቦለድ ባህሪያት” እና “የቃለ ጉባኤ አያያዝ” የሚለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በቀጥታ ወደ ማብራሪያ በመግባት ገለፃ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በኃላ በተጨማሪነት ስለ ቃለ ጉባኤ አያያዝ በተደራቢነት ያስተማሩ ሲሆን ተማሪዎችም ከመጀመሪያው ርዕስ ይልቅ በሁለተኛው ርዕስ ላይ የተሻለ ተሳትፎ ሲያደርጉ አጥኚው ተመልክቷል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው አንድም ተማሪዎች ምን ጊዜም የሚቀርብላቸውን ከሚያውቁትና ከሚረዱት ነገር በመነሻነት ማስጀመሩ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያመለክት መሆኑን እና ተማሪዎቹ ስለ መጀመሪያው ርዕስ በቂ የሆነ ግንዛቤ ከዚህ በፊት ያላገኙ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህን በተመለከተ Elizzabeth (1982፡12) እንዲህ በማለት የገለጹትን ጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ይመስላል ፡፡

“በተመረጠው ይዘት ላይ ተማሪዎች የሚያውቁትን ለይቶ ማውጣት” ተማሪዎቹ ሊረዱት የሚችሉትን አለማገናዘብ ደግሞ የታቀደውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ አሰቸጋሪ መሆኑ የታመነ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተመጠነና ውስን አላማ ያለው እና በተመደበለት ክፍለ ጊዜ ውስጥ መምህራኑ በዕለቱ ሊያከናውኗቸው ያቀዷቸውን ተግባራት በአጠቃላይ አጠናቀው መውጣት ሲችሉ ነው ዕቅዱ ግቡን መትቷል ማለት የሚቻለው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ክፍለ ጊዜ የተከናወነው ተግባር ከርእሱ ስፋትና ተደራራቢነት የተነሳ ተማሪዎች ጥያቄ ለመጠየቅ ዕድል ሳያገኙ ከመቅረታቸውም ባሻገር የማጠቃለያ ሃሳብ እና ተማሪዎቻቸውን የመገምገም ተግባር ለማከናወን የሰአት እጥረት እንዳጋጠማቸው መመልከት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አንድ መምህር የትምህርቱን ይዘትና አላማ ሲነድፍ የተመጠነና ሊለካ ወይም ሊገመት በሚችል መንገድ ማከናወን ስላለበት በተቻለ መጠን አላማውን ውስን በማድረግ ወደ ተፈለገው ግብ መድረስ ተገቢ ነው፡፡

ይህን በተመለከተ Ray (1969፡19) የመማር ማስተማር ዓላማ በግልፅ መስፈር እንዳለባቸው ሲያብራሩ “በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ የሚፃፉ ዓላማዎች ውስንና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ ወይም የተማሪዎችን የባህሪይ ደረጃ የሚገመግምና የሚያስፈልገውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሆን አለባቸው” ይላሉ፡፡ በተጨማሪም Ray (1969፡24) “መምህሩ በሚያዘጋጀው የዕለት ተዕለት የትምህርት ዕቅድ አነዳደፍ የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ ጥያቄዎች መመለስ እንዲችል ሆኖ ቢዘጋጅ ተመራጭነት ይኖረዋል” ይላሉ፡፡

ዓላማዎቹ በክፍል ውስጥ የተማሪውን ፍላጎት ችሎታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ መሆናቸውን፣ ዓላማዎቹ የተወሰኑና ከሚፈለጉት ባህሪያት ከተጠቃሚ ዕሴቶች ወይም ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያላቸው መሆኑን፣ ዓላማዎቹ በሐሳብ፣ በምልክት፣ በእሴት፣ በልምድ ወይም በስሜት መገለጽ መቻላቸውን እና ለስኬማነታቸው ለተማሪው የባህርይ ብቃት በማስገኘት በጎ/አበረታች/ የባህሪይ ለውጥ በማምጣት የሚረዱት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የተዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ አላማዎች ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ ሊያመጡ የሚፈለገውን ግብ ከማሳካት አንጻር ሲታይ ግን የተሻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም በየዕለቱ ማስተማር የሚገባውን ትምህርት በተመለከተ አስቀድሞ ዓላማ መንደፍ አለበት፡፡ ለተማሪው በዕለቱ ማቅረብ የሚገባውን ትምህርትና የሚጠበቅበትን የባህሪይ እና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት የመማር ማስተማር ዓላማዎች በተገቢው ሁኔታ መነደፍ አለባቸው፡፡ አነዳደፋቸውን በተመለከተ Elizzabeth (1982፡13) ሲያስረዱ "የመማር ማስተማር ዓላማዎች መገለፅ ያለባቸው ተማሪዎች በወቅቱ የተመደበላቸውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣ የተማሩትን እንዴት መተግበር አለባቸው ከሚለው አንፃር መሆን አለበት፡፡ የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ስንነድፍ ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ ተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ ማስቀመጥ እንጂ መምህሩ ምን ማድረግ እንዳለበት ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡" ይላሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ ያየናቸው የትምህርት ዕቅድ አላማዎች ተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የሚያስረዱ በመሆናቸው አላማውን በወረቀት ላይ በማስፈር ረገድ ብዙም ችግር ያለበት አይመስልም፡፡

በሁሉም አስረኛ ክፍል ተደልድለው የሚያስተምሩ መምህራን የሚያዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች የትምህርት ቤቱንና የመምህሩን ስም፣ የትምህርት ዓይነት፣ ክፍል፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን፣ የትምህርቱ ርዕስ፣ የትምህርቱ ዓላማ፣ የክፍለ ጊዜው ርዝመት፣ የርዕሱ ዝርዝር ተግባር፣ የመምህሩና የተማሪው ተግባር፣ የክፍል አደረጃጀት፣ ክትትል ግምገማና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ያካተተ ነው፡፡ የዕለታዊ ዕቅድ ማቅረቢያው ቅጽ ይህን ይዘት ቢኖረውም ከቅርጽ አንጻር ስንመለከት ግን ልዩነቶች ይታዩበታል፡፡ ይኸውም የዲምቱ እና የአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ሲሆን በተቀሩት ሶስት ትምህርት ቤቶች ያለው እቅድ ግን እያንዳንዱ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ወጥ የሆነ የዕቅድ ማዘጋጃ ቅጽ አለመኖሩን ነው፡፡ ይህ ደግሞ መምህራን የሚያዘጋጁአቸው ዕቅዶች ተመሳሳይነት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ በመሆኑም የመምህራኑ የዕቅድ ትግበራም መምህራኑን አተገባበራቸውን እንዲለያይ ያደረጋቸው መሆኑን ያሳየናል፡፡

ምክንያቱም የእያንዳንዱን ትምህርት የዕቅድ ቅርጽ ብንመለከት ልዩነቱን በጉልህ መረዳት ይቻላል፡፡ በናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተዘጋጀው የዕቅድ ቅርጽ የትምህርት ቤቱ ስም፣ ክፍል፣ የትምህርት አይነት፣ ቀን፣ ክፍለ ጊዜ፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የትምህርቱ ዓላማ፣ የአስተማሪው ተግባር ብሎ በስሩ (መግቢያ፣ አቀራረብ፣ ማጠናከሪያ፣ ምዘና)፣ የተማሪው ተግባር፣ መርጃ መሳሪያ እና አስተያየት የሚሉትን ይዘቶች የያዘ ነው፡፡

የአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ የሚከተለውን አይነት የቅርጽ ይዘት አለው፡፡ የመምህሩ ስም ፣ የትምህርት ዓይነት፣ ክፍል፣ ትምህርት ዓይነት፣ የትምህርቱ ርዕስ፣ ቀን፣ ክፍለ ጊዜ፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የመምህሩ ሚና፣ የተማሪው ሚና፣ የማስተማር ዘዴ ፣ የሚያዳብሩት ክሂል፣ መርጃ መሳሪያና ምርመራ በሚሉት ይዘቶች የተከፋፈለ ነው፡፡

የዲምቱ እና የአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዕቅድ ቅርጽ ተመሳሳይ ሲሆን ይዘቱም የሚከተለው ነው፡፡ የትምህርት ቤቱ ስም ፣ የመምህሩ ስም፣ የትምህርት አይነት፣ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ክፍል፣ ቀን፣ ክፍለ ጊዜ፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የትምህርቱ ዓላማ፣ የመምህሩ ተግባር፣ የተማሪው ተግባር፣ የክፍል ቅንጅት፣ ምዘና፣ መርጃ መሳሪያ እና አስተያየት በሚል የተከፋፈለ ነው፡፡

በመጨረሻ የምንመለከተው የዕቅድ አዘገጃጀት ቅርጽ የገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ይሆናል፡፡ የዚህ ትምህርት ቤት የዕቅድ ቅርጽም ከሌሎቹ ትምህርት ቤቶች የተለየ ነው፡፡ ይኸውም የትምህርት ቤቱ ስም፣ የመምህሩ ስም፣ ቀን፣ የትምህርት አይነት፣ ክፍል፣ ርዕስ፣ ዝርዝር ዓላማ፣ ጊዜ፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የመምህሩ ተግባር፣ የተማሪው ተግባር፣ የማስተማሪያ ዘዴ፣ መርጃ መሳሪያ እና ምርመራ በሚል የተከፋፈለ ይዘት ያለው የዕቅድ ቅርጽ የያዘ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህንን በአግባቡ ለመረዳት መረጃውን ተጨባጭ ለማድረግ ሲባል በአባሪነት የቀረበውን የትምህርት ቤቶቹን የዕቅድ ቅጾች መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህን መመልከቱ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት የሚዘጋጁት ዕቅዶች ወጥ የሆነ የአዘገጃጀት ሂደት ያልተከተሉ በመሆናቸው የየትምህርት ቤቶቹ አተገባበር የተለያየ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የእቅድ አዘገጃጀታቸውንም ስንመለከት በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ከሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ውጪ በመምህሩ ትግበራ ወቅት መከናወን የነበረበት ተግባር በግልጽ ሰፍሮ አይስተዋልም፡፡ ይህም ማለት መምህራን የሚያዘጋጁቸው የትምህርት ዕቅዶች ባሉበትም ሆነ እነሱ በሌሉበት ቦታ ሌላ አካል በቀላሉ ተረድቶት ወደ ተግባር ሊለውጠው የሚችል መሆን ነበረበት፡፡ በገበራ ሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ አንድ መምህር ግን በትምህርት ዕቅድ ይዘታቸው ውስጥ ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት በእቅዳቸው ውስጥ አስፍረዋል፡፡ ይህ መሆኑ የትምህርት ዕቅድን በቀላሉ ወደ ተግባር ለመለወጥ ይቻል ዘንድ በመምህሩ ትግበራ ውስጥ ለመነሻ የሚሆን ጥያቄያዊ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን በማስገባት

መገልገል ትግበራውን ስኬታማ ሊያደርገው ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በቀን 19/07/2008 በተጠቀሰው ትምህርት ቤት የተስተዋለውም ይኸው እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ይልቅ ዝርዝር ርዕሰ ጉዳይን የሚይዙ መሆናቸው ከምሁራን ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተዘጋጀው ዕቅድ አላማ ውስጥ አልፎ አልፎ አጠቃላይ አላማ ሲቀመጥም ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ተማሪዎቹ ይህን ትምህርት ተምረው ሲያጠናቅቁ ያውቃሉ፣ ይረዳሉ፣ ወዘተ ተብለው የተገለፁ በመሆናቸው ከዚህ ይልቅ ያብራራሉ፣ ይናገራሉ፣ ያስረዳሉ፣ ይገልፃሉ በሚሉት ቢገለፁ ዝርዝር የመማር ማስተማር ዓላማዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በዝርዝር ዓላማ መቀመጥ እንዳለበት እና መሻሻል እንደሚገባው ጠቋሚ ሲሆኑ በተቀሩት ትምህርት ቤቶች የተዘጋጀው ግን ከዚህ አንፃር የተሻለና ሊበረታታ የሚገባው እንደሆነ አጥኚው ተረድቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዕለታዊ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት መነደፍ የሚገባቸው አላማዎች ውስንና ግልፅ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑና ተማሪዎችን በቀላሉ ለመገምገም የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው ተመራማሪዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህን በተመለከተ በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው መሠረት ያስተማሩትን በመመዘን የሚያዘጋጁት መመዘኛች ለተማሪዎቹ ሲቀርቡ ምን ዓይነት ሥርዓት መከተል እንደሚገባቸው Ray (1969፡26) እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ "መመዘኛዎቹ ግልጽና የተመጣጠኑ መሆን አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰሩትን ጠንቅቀው እንዲያውቁ መመሪያዎችን በግልፅ ማሳወቅ ለምን እና እንዴት እንደሚሰሩ ተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን ሰርተው ካበቁ በኃላ በሥራቸው ላይ ለመወያየት ክፍለ ጊዜ መወሰን በመጨረሻም ከመካከላቸው ለሚፈጠረው ልዩነት የሚረዳ ውጤት መስጠትም የተገባ ነው፡፡" ይላሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እንኳን በቀላሉ ተረድተው ለውጤታማነት ራሳቸውን ሊያዘጋጁ ይችላሉ ለማለት የቀረበ ሃሳብ ይመስላል፡፡

ከዚህ ሌላ የትምህርት ቤቶቹ ዕቅድ አዘገጃጀት ሲፈተሽ የተስተዋለው ችግር ለሁለት ቀናት የሚዘጋጁት ዕቅዶች በሁሉም ትምህርት ቤቶች በአንድ ወረቀት ላይ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ ይሁንና በአንድ ወረቀት ላይ የሚዘጋጀው ዕቅድ ይህን ይዘት ያለው መሆኑ የሚደገፍ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም የትምህርት ዕቅድ ለመምህሩ እንደ መርጃ መሳሪያ የሚቆጠር በመሆኑ ለየዕለቱ የሚታቀደው የትምህርት ዕቅድ በተለያየ ወረቀት ላይ ቢዘጋጅ

የተሻለ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ወረቀት ላይ የሚታቀደው ዕቅድ የትምህርቱ ይዘት እና የትምህርቱ አላማ ለሁለቱም ቀናት ወጥ ሆኖ ሲዘጋጅ እንደነበረ ለማየት ተችሏል፡፡

ይህንንም በአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀን 17/08/2008 እና በ18/08/2008 በተደረገው ምልከታ የተስተዋለው ለዚህ ሃሳብ ማሳያ ይሆናል፡፡ በሁለቱ ምልከታ ለመረዳት የተቻለው ዕቅዱ ሲዘጋጅ የትምህርቱ ይዘት፣ የትምህርቱም አላማ ዕቅድ ወጥ ሆኖ ነው፡፡ ይህ ማለት የትምህርቱ ይዘትም ሆነ አላማ ለየዕለቱ አልተከፋፈለም፡፡ ይህ የሚያሳየው በአንድ ዕለት ለአንድ ክፌለጊዜ መታቀድና መተግበር ያለበት ዕቅድ በአንድ ላይ ሳይከፋፈል መቀመጡ የዕለታዊ ዕቅድ ዝግጅትን ሂደት የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም በየዕለቱ የሚታቀደው ዕቅድ ውስንና ወደ ተፈለገው ግብ ሊያደርስ የሚችል ሆኖ መታቀድ ያለበት ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም በየዕለቱ የምንጠቀመው የማስተማር ስልት ለየእለቱ የተለያየ ቢሆን መሰላቸትን የሚቀንስ ይሆናል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች እንደ ትምህርቱ ጠባይና ባህሪይ ተለዋዋጭ ከሆነ አርኪ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ Harmer (1991፡221)፡፡ ተማሪዎች አንድ ዓይነት ለሆነና የማይለወጥ የማስተማሪያ ዜዴ በተደጋጋሚ የሚጋለጡ ከሆነ ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቅረፍ የመማር ማስተማሪያ ዜዴውን ሁልጊዜ ተለዋዋጭና ማራኪ ለማድረግ አስቸጋሪ ቢሆንም በተቻለ መጠን በተለያዩ የማስተማሪያ ዜዴዎች በመጠቀም ተማሪዎችን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተማሪዎቹ ዘንድ የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን የማከናውን ፍላጎት ሊጨምር ይችላል፡፡

Borich (1988፡100፣ 117፣ እና 128) በተለያዩ ዜዴዎች መጠቀም ጠቃሚ እንደሆነ ሲገልፁ አንድ መምህር ለተማሪዎቹ ውጤታማ የሆነና እውቀት ለማስጨበጥ የማስተማር ሂደቱን ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ትምህርቱን ከየት መጀመር እንዳለበት ማጤንና የተማሪውን የማወቅ ደረጃ በሚመጥን መልኩ የተለያዩ የማስተማሪያ ዜዴዎችን ተጠቅሞ ተማሪዎችን በዕውቀት ማነፅ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተግባራዊ የሆነ ውጤታማ የትምህርት ሥራ ለመስራት የሚችሉ ለቋንቋ ትምህርት ዕቅድ የተዘጋጀውን የአሰጣጥ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ዜዴዎችን ተጠቅመው ተግባራዊ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምልከታ የተደረገላቸው የአኮ ሁለተኛ ደረጃ መምህር በዕቅድ ትግበራቸው ወቅት ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያደርጉት የነበረው ጥረት የሚያበረታታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዕቅድ ዝግጅታቸው መሻሻል ያለበት እንደሆነ ከላይ በተገለፅው የምልከታ ሂደት መቃኘት አለበት የሚል የዚህ ጥናት አቅራቢ ሃሳብ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የዕቅድ አዘገጃጀቱን አጥኚው ለመቃኘት እንደሞከረው በሁሉም ክፍሎች በተዘጋጁት ዕለታዊ ዕቅዶች ውስጥ የትምህርቱ ዓላማ ውስን ቢሆንም በኦሞናዳና በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁለት መምህራን ያዘጋጇቸው ሁለት ዕቅዶች አላማ ሁለት እና ከዚያ በላይ በመሆኑ የተማሪዎቹን የባህሪይ ለውጥና ደረጃ በቀላሉ ለመገምገም የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀን 14/07/2008 በ10ኛ D ክፍል በተደረገው ምልከታ ሁለት እራሳቸውን ችለው አላማ ተነድፎላቸው ሊተገበሩ የሚችሉ ርዕሶች በአንድ ይዘት ስር ተካተው ተስተውሏል፡፡ ርዕሶቹም ምዕላዶች፣ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት የሚሉት ናቸው፡፡ እንዲሁም ከላይ እንዳየነው በናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀን 15/07/2008 በ10ኛ D በተደረገው ምልከታ የአጭር ልብወለድ ባህርያትና የቃለ ጉባኤ አያያዝ የሚሉ ሁለት ርዕሶች በአንድ ዕለት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተገኝቷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የታቀደውን ዕቅድ ለመተግበር ከመፈለግ በዘለለ ተማሪዎቹ በዕለቱ መጨበጥ የሚገባቸውን ዕውቀት ያለመመጠንን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ በትምህርቱ ይዘት በአንድ ክፍለ ጊዜ ሊጠናቀቅ የማይችል ከመሆኑ ባሻገር ከተማሪዎቹም የሚፈለገውን የዕውቀት ግብአት የማያስገኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ በመሆኑም መምህሩ ለዕለቱ ያዘጋጁትን ዕቅድ ባዘጋጁት መሰረት ለማጠናቀቅ መቸገራቸውን በዕለቱ በተደረገው ምልከታ ተረጋግጧል፡፡ ምክንያቱም የአጭር ልቦለድ ባህርያት የሚለው ርዕስ ብቻውን ሰፊ ርዕስ በመሆኑና በአንድ ክፍለ ጊዜ እራሱን ችሎ መጠናቀቅ የሚገባው ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ በተደራራቢነት በአንድ አላማ ስር መነደፍ የሚገባቸው የትምህርት ዕቅዶች ንዑሳን ርዕሶች ቢሆኑ ይመረጣል እንጂ ሰፋፊና የተለጠጡ መሆን እደሌለባቸው አመላካች ነው፡፡

በአጠቃላይ በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን ጠቅለል አድረጎ መመልከቱ አሰፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ትምህርት ቤት ለሁለት መምህራን በተደረገው ስድስት ምልከታ በክፍል ውስጥ ሲከናወን የነበረውን የዕቅድ አተገባበርን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩት መምህራን አማርኛ ቋንቋን በንዑስነት የተማሩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ በትምህርት ቤቱ በአራት ክፍል ውስጥ ተደልድለው የሚያስተምሩትም ሁለት ሁለት ክፍሎችን ይዘው ዕለታዊ ዕቅዳቸውን አቅደው የሚተገብሩ መሆኑን ነው፡፡

የዕቅዱን ዝግጅትና ቅርፅ በተመለከተ የትምህርት ቤቱ ስም፣ የትምህርት ዓይነት ፣ መምህሩ ስም፣ ክፍል፣ ዝርዝር ዓላማ፣ ርዕስ፣ ጊዜ፣ ቀን፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የመምህሩ ተግባር፣ ተማሪው ተግባር፣ የማስተማሪያ ዘዴ፣ መርጃ መሳሪያና ምርመራ የሚል የቅርጽ ይዘት ያለው ነው፡፡ በዚህ እቅድ ቅርፅ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅርፅ መያዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በመምህሩና በተማሪው ተግባር እንዲሁም የማስተማር ዘዴ ውስጥ የሚሰፍሩት ቃላትና ሀረጋት በሁለቱም መምህራን ዕቅድ ውስጥ ተመሳሳይና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ በምሳሌነት ብናነሳ በመምህሩ ተግባር ውስጥ ያለፈውን ትምህርት መከለስ ፣ማብራሪያ መስጠት፣ እንዲይጠቁ ማበረታታት፣ መጠየቅ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በተማሪዎቹ ተግባር ውስጥም ያለፈውን ያስታውሳሉ፣ የሚሰጠውን ማብራሪያ ይከተላሉ፣ ይጠይቃሉ፣ ይመልሳሉ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ዕቅዱን ወደተግባር በማሸጋገር ወቅት ቀለል ባለ መንገድ ሰዎች ተረድተው ለመተግበር አስቸጋሪ መስሎ ይታያል፡፡ ምክንያቱም ዕቅዱ በአንድ ወረቀት ላይ ለሁለት ቀናት ተከፍሎ የታቀደ መሆኑ ሲሆን እንደ መሪ ጥያቄና በመነሻነት የዕለቱን ትምህርት ምን ምን ነገሮችን አቅፎ ወይም ትኩረት አድርጎ ለማስተማር እንደታቀደ ጠቋሚ ነገር የለውም፡፡ ከዚህ በተጎዳኝ በማስተማር ዘዴ ውስጥ መምህራኖቹ ያሰፈሩት በገለፃ መልክ በጥያቄና መልስ በሚሉ ሀረጋት ነው የጠቆሙት፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹን በቡድን በማቀናጀት የሚከናወን ተግባር አለመኖሩን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የታቀደውን ዕቅድ በሚፈለግ መልኩ ከግብ ለማድረስ አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ መምህር የሚያዘጋጀውን ትምህርት ከግብ ለማድረስ የተማሪው ተሳትፎ ወሳኝ ስለሆነ ነው፡፡

በሌላ መልኩ በዚህ ትምህርት ቤት የታቀደውን እቅድ ለትምህርቱ የተሰጠውን ክፍለ ጊዜ ክፋፍሉ ማስቀመጡን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም ለመግቢያ፣ ለአቀራረብ፣ ለማጠናከሪያ ለምዘና በማለት ከፋፍሎ አስቀምጧል፡፡ በዚህ መልኩ መቀመጡ የሚመከርና የሚገባ ነው፡፡ ምክንያቱም የታቀደውን ዕቅድ ለየትኛው ትምህርት አቀራረብ ወይም ትምህርት

አሰጣጥ መንገድ ጠቋሚ ስለሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተቀመጡት ደቂቃዎች የትኞቹን ይዘቶች ለማስተማር እንደሆነ የመምህሩን ተግባር ወይም የተማሪውን ተግባር ከፋፍሎ ያላስቀመጠ እንደሆነ አጥኚው ተረድቶአል፡፡ በአጠቃላይ መምህራኑ ያቀዱትን እቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅዶች እና ምልከታው እስከታየበት ጊዜ ድረስ የደረሱበት ርዕስ በአመት ውስጥ ለማስተማር ያቀዱትን ዕቅድ ያጠናቅቃሉ ብሎ ማሰብ እንደማይቻል ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.2.2. የትምህርት ዕቅድ ይዘት ትንተና

የትምህርት ዕቅዱ ይዘት The Modeline Hunter lesson Design modelን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ የዚህ ሞዴል መሰረታዊ ይዘቱም የሚከተሉትን ፅንሰ ሀሳቦችን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ጥሩ የማስተማር እቅድ ይዘት ስምንት መስፈርቶች አሉት እነሱም የሚከተሉት ናቸው ይላል፡፡

- ዋና የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከተማሪዎቹ ማስታወሻ እንዲይዙ ማበረታታት ወይም ማስታወሻ መያዣ ማደል፤
- የክለሣ ጥያቄ ሰሌዳ ላይ መጻፍ፤ .
- የእለቱን ትምህርት ምን መሆን እንደሚችል በምን አይነት ሁኔታ እንደሚከተታሉ ከግብረ መልስ የተወሰነ አላማ ማገናኘት፤
- የትኛውን ክሂል ለማሣደግ እንደተፈለገ መረዳት፤
- ተማሪዎችን በተገቢ ሁኔታ ማለማመድ የሶስትዮሽ ልምምድ ማስደረግ በሥራ ማሣየት፤
- ተማሪዎችን በስድስት ስድስት በማቀናጀት መጠቀም፤
- መከታተላቸውን ማስተዋል፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን ወስኖ መስጠት፤
- ክለሣ በማድረግ የተማሩትን በግል መጠየቅ፤ ዛሬ ምን ተማራችሁ (ንገሩኝ፣ አሣዩኝ...) በማለት ማበረታታት ተገቢ ነው ይላል፡፡

  htt;//www.adprima.com/w/05.htm. the Modeline Hunter lesson Design model.

በዚህ ሞዴል የተገለጸው የትምህርት ይዘት በትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚገኙትን የዕቅድ አካላት ሁሉ የሚመለከት መስፈርት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም መስፈርቱ

ተማሪዎቹን በምናስተምርበት ወቅት መምህሩ ማከናወን የሚገባውን የመምህር ተግባራትን ጭምር የሚገለጽ ስለሆነ ነው፡፡ በማሳያነት ብንወስድና የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከተማሪዎቹ ማስታወሻ እንዲይዙ ማበረታታት ወይም ማስታወሻ መያዣ ማደል፤ የክለሣ ጥያቄ ሰሌዳ ላይ መጻፍ የሚለው የትምህርቱን መግቢያ (Introduction)ን የሚመለከት ነው፡፡ የእለቱን ትምህርት ምን መሆን እንደሚችል በምን አይነት ሁኔታ እንደሚከተታሉ ከግብረ መልስ የተወሰነ አላማ ማገናኘት፤የትኛውን ክሂል ለማሣደግ እንደተፈለገ መረዳት፤ ተማሪዎችን በተገቢ ሁኔታ ማለማመድ የሶስትዮሽ ልምምድ ማስደረግ በሥራ ማሣየት፤ የሚሉት የሞዴሉ መስፈርት ደግሞ በትምህርት አቀራረብ (presentation) ወቅት መምህሩ ማከናውን የሚገባውን ተግባራት የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎችን በስድስት ስድስት በማቀናጀት መጠቀም፤ የሚለው መምህሩ በዕቅዱ ውስጥ ማከናወን የሚገባውን የክፍል ውስጥ ቅንጅትን የሚመለከት ነው፡፡ ሌላው የሞዴሉ መስፈርት ደግሞ መከታተላቸውን ማስተዋል፤ የተለያዩ ጥያቄዎችን ወስኖ መስጠት፣ ክለሣ በማድረግ የተማሩትን በግል መጠየቅ፤ ዛሬ ምን ተማራችሁ (ንገሩኝ፣ አሣዩኝ...) በማለት ማበረታታት በትምህርት ዕቅዱ ውስጥ መከናወን ያለበትን ማጠናከሪያ (stabilization) ወይም ክለሳ እና ለተማሪዎቹ መደረግ ያለበትን ምዘና(Evaluation) የሚመለከት ነው፡፡

ይህን ሞዴል መሰረት በማድረግ የትምህርት ዕቅዱን አዘገጃጀት እና አተገባበር በአግባቡ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ በሚከናወን የክፍል ምልከታ በመሆኑ ከምልከታው የተገኘው መረጃ ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 4.2.3. ስር ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

### 4.2.3. ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

የክፍል ውስጥ ምልከታ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ለማጠንከር እና በክፍል ውስጥ የሚደረገውን የዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን ለማረጋገጥ ሲባል በስራ ላይ ውሏል፡፡ ይህንንም ለማከናወን ሲባል አጥኚው በናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣በጢሮ አፈታ ወረዳ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት፣ አኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት ፣ ገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት ክፍሎችን በድምሩ አስር 10ኛ ክፍሎችን በእጣ ንሞና በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ ክፍል

ጊዜ በክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታ አካሂዷል፡፡ እያንዳንዱን ክፍል ለሶስት ሶስት ዙር በድምሩ ለሰላሳ ጊዜ አስራ አምስት መገምገሚያ መስፈርቶችን የያዘ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በባለ ሁለት ድርድር (አዎ/አይደለም) የጥያቄ አቀራረብ ስልት በመጠቀም ምልከታ አካሂዷል፡፡ ጥያቄዎቹ በሶስት ክፍል የተከፈሉ እና የአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበርን ለመፈተሽ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ውጤት እንደሚከተለው በተዘጋጀው ቼክ ሊስት በመታገዝ እንደየምድባቸው በመግለጽ ተተንትኗል፡፡ ለክፍል ምልከታ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በተለያየ ምድብ ማስቀመጥ የተፈለገበት ምክንያት በተለያዩ ሶስት ምድቦች የተከፈሉትን የመከታተያ መገምገሚያ መስፈርቶች በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል ለማድረግ ነው፡፡ ምድቦቹም የዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክተው የተዘጋጁ የዕቅድ አተገባበርን አስመልክተው የተዘጋጁ እና የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በተመለከተ የተዘጋጁ መገምገሚያ መስፈርቶች በማለት በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ተከፋፍለው የቀረቡ ናቸው፡፡

በነዚህ ምድቦች የቀረቡት መገምገሚያ መስፈርቶችም ጥናቱ በተከናወነባቸው ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያዘጋጁትን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማሳየት ያግዛል ተብሎ የታመነበት ስለሆነ የቀረበ ነው፡፡

የዕቅድ አዘገጃጀትን አስመልክቶ በአንድ ተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የተመደቡት መገምገሚያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. መምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ?
2. መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ይገባሉ?
3. መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ ነው?
4. ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት አለው?
5. መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት አለው?

እንደሚያመለክተው መምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት በአጠቃላይ ከተደረገው ሰላሳ የክፍል ምልከታ ውስጥ አስሩ አዎ

አዘጋጅተው ይጠቀማሉ የሚል ሲሆን ሃያው ግን ያዘጋጃሉ ቢያዘጋጁም በዕቅዱ ግን አይጠቀሙበትም የሚል ምላሽ የያዘ ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ ነገር ግን ባዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ በተግባር የሚጠቀሙበት ጥቂቶቹ ብቻ መሆኑን ነው፡፡

መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ይገባሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ ስምንቱ አዎን የሚል ሲሆን ሃያ ሁለቱ ደግሞ መምህሩ ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው የማይገቡ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ዕቅዱን ከማዘጋጀት በዘለለ በክፍል ትግበራ ወቅት ወደ ክፍል ይዘው በመግባት የማይገለገሉበት መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል፡፡

መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ ነው? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት አስመልክቶ ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ አምስቱ አዎ የሚል ሲሆን የሃያ አምስቱ ምልከታ እንደሚያመለክተው ደግሞ መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕቅድ አላማውን ከግብ ያደረሰ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ማለት መምህራን ባቀዱት እቅድ መሰረት የማይተገብሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከተደረገው ምልከታም መረዳት የተቻለው መምህራኑ በትምህርት እቅድ ላይ በአላማ ነድፈው በዕቅዳቸው ላይ ካሰፈሩት ሃሳብ ውጪ በሌላ ክፍለ ጊዜ አላማ ተነድፎለት ሌላ ርዕስ ሊሆን የሚችል ርዕስ በተደራቢነት ሲተገብሩ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ምናለባት መምህራኑ ያቀዱትን ዕቅድ በተሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ለማጠናቀቅ ከመሻት በዘለለ ሊኖረው የሚችል ጥቅም ይኖራል ብሎ መናገር አስቸጋሪ ይመስላል፡፡

ከክፍል ምልከታው ሁለቱ መምህራኑ ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት ያለው መሆኑን ሲያመለክት ሃያ ስምንቱ ደግሞ መምህራኑ ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ መምህራን የሚያዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ ዕቅዱን ለመተግበር የሚፈልግ ሌላ አካል በቀላሉ ተረድቶ ወደ ተግባር ሊያሸጋግረው የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል፡፡

መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት አለው? ለሚለው የክፍል ምልከታ መገምገሚያ መስፈርት ሁለቱ አዎ የሚል

ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ስምንቱ ደግሞ መምህሩ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ማለት መምህራኑ አቅደው እየተገበሩ ያለው ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ቀድሞ እየተተገረ መሆኑን አሊያም ከአመታዊ ዕቀዱ ወደኋላ ዘግይተው እየተገበሩ መሆኑን የሚያሳ መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታም ሆነ በተከናወነው የሰነድ ፍተሻ መምህራኑ እየተገበሩ ያሉት የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ወደኃላ የቀሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚነሳው ከላይ እንደተጠቀሰው ለትምህርቱ የተሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ከትምህርቱ ይዘት ጋር የማይመጣጠን መሆኑ ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አብዛኛውን ጊዜ መምህራኑ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ያለመጠቀም፤ ቢያዘጋጁም ያዘጋጁትን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ወደ ክፍል ይዘው ያለመግባት፤ መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕቅድ በሚፈለገው መልኩ አላማውን ከግብ ያደረሰ አለመሆኑ፤ ያዘጋጁት ዕቅድ ከቋንቋው ባህሪይ አንጻር ግልፅነት የሚጎለው መሆኑን እና መምህራኑ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት የሌለውና በተፈለገው ወቅት መጠናቀቅ የማይችል መሆኑን የሚያሳ ነው፡፡

Elizzabeth (1982፡12) ስለ ትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ ሲያስረዱ “አጠቃላይ የትምህርት አካሄድ በእቅድ ላይ የተመሰረት በመሆኑ እቅድ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ይኖረዋል፡፡” ይላሉ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ Dorothy (1985፡48) ስለዚህ እቅድ ሲናገሩ “የትምህርት እቅድ ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ሂደት እንደ መሳሪያ ወይም መርጃ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለጥሩ የማስተማር ሂደት አስፈላጊና እንደመርህም ይጠቅማል” ይላሉ፡፡ ይህ ማለት የመማር ማስተማርን ሂደት ያለ ዕቅድ ስኬታማ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ በመሆኑም የትምህርትን ሂደት ከግብ ለማድረስ ዕቅድ ወሳኝና ዋነኛ የመምህሩ ተግባር መሆኑን ማወቅና መተግበር ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

የዕቅድ አተገባበርን አስመልክቶ በአንድ ምድብ ውስጥ ተመድበው ምልከታ የተደረገባቸው መገምገሚያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. መምህሩ ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት ይተገብራሉ?
2. መምህሩ የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ያደርጋሉ?
3. ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ ይተገብራሉ/ያጠናቅቃሉ?
4. መምህሩ ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ይጠቀማሉ?
5. መምህሩ የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ ይከልሳሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በአንድ ምድብ ስር በማድረግ ምልከታ ተከናውኖበታል፡፡

ከላይ መምህሩ ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት ይተገብራሉ? ተብሎ ለቀረበው መገምገሚያ መስፈርት ከክፍል ምልከታው ውስጥ ሁለቱ አዎ የሚል ሲሆን ሃያ ስምንቱ አይደለም የሚል ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ባዘጋጁት የትምህርት እቅድ መሰረት መተግበር የማይችሉ መሆኑን የሚሳ ነው፡፡ ከተደረገው የክፍል ምልከታ ውስጥ አስራ አራቱ መምህሩ የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ያደርጋሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት አዎ ያደርጋሉ የሚል ምላሽ ያስገኙ ሲሆን ስድስቱ አያደርጉም የሚል ምላሽ ነው ያስገኙት፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው መምህራን መምህራኑ የትምህርቱ ዕቅድ ይሳካ ዘንድ የተቻላቸውን ጥረት ማድረግ የሚችሉ መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ በመቀጠልም መምህራን ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ ይተገብራሉ/ያጠናቅቃሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት ሁለቱ አዎ ይተገብራሉ የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ስምንቱ አይደለም አይተገብሩም ወይም አያጠናቅቁም የሚል ምላሽ አስገኝቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው መምህራን ባቀዱት ሰአት ዕቅዳቸውን ወደ ተግባር እንዳይለውጡት እንቅፋት የሚሆንባቸው ነገር እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በቀጣይነት በክፍል ምልከታው የተስተዋለውና ለመከታተያ ከተዘጋጀው መገምገሚያ መስፈርት ማግኘት የተቻለው ምላሽ መምህሩ ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ይጠቀማሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት ሁሉም ወይም ከሰላሳው ምልከታ ምንም አይነት የመርጃ መሳሪያ መምህራኑ እንደማይጠቀሙ ለማየት ተችሏል፡፡ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም ደግሞ መምህራን ያቀዱትን ዕቅድ ወደ ተግባር ለማሸጋገር ወሳኝ መሆኑን ተመራማሪዎች እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህን የትምህርት መረጃን በተመለከተ Sells (1981፡268) በመማር ማስተማር ሂደት ስለማስተማሪያ ቁሳቁሶች አስፈላጊነት ሲገልፁ ለትምህርት መስጫነት የተለያዩ ዓይነት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በትምህርት ሂደት ላይ መሠረታዊ ምርምርን

ይፈጥራሉ፡፡ ሀሳቡን ይሰበስባሉ፡፡ ፍላጎትን ይቀሰቅሳሉ፣ መረዳትን ይጠናክራሉ፣ ዝምድናን ያፀናሉ፣ ትዝታን ይፈጥራሉ፣ ሀሳብን ያነሳሳሉ በተጨማሪም የምንማረውን ትምህርት በማጠናከር ጊዜንና ሀይልን ይቆጥባሉ ይላሉ፡፡

የቋንቋ መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ጥሩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማስፈራቸው ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በተገቢው ጊዜና ቦታ የመጠቀምና የተነደፈውን የመማር ማስተማር ዓላማ ግብ ማስገኘት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ መምህራን በተገቢው መንገድ መቼ እንዴትና ምን ወይም የትኛውን ቁሳቁስ ለየትኛው ትምህርት ተገቢ ነው የሚለውን ማወቅ አለባቸው፡፡ Sells (1981፥263) ትክክለኛ የሆነ የማስተማሪያ ቁሳቁስ በትክክለኛው ጊዜና ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ የምንረዳው መምህራን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአግባቡ ቢጠቀሙ ዕቅዳቸውን በሚፈለገው መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸው መሆኑን ነው፡፡

የዕቅድ አተገባበርን አስመልክቶ ከክፍል ምልከታ ምልከታ የተገኘው ሌላው የትግበራ ጥያቄ ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡ መምህሩ የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ ይከልሳሉ? የሚል ሲሆን የአራት መምህራን ተግባር በአዎንታዊነት የታየ ሲሆን የሃያ ስድስቱ መምህራን ትግበራ ደግሞ አሉታዊ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ለመከለስ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ባላቸው ጊዜ በመጠቀም የዕለቱን ትምህርት ለመሸፋን ከማሰብና ያላቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆን ያሳደረባቸው ተጽዕኖ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያለው ሀሳብ እንደሚያመለክተው የመምህራን የዕቅድ አተገባበር ምን እንደሚመስሉ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የመከታተያ ጥያቄዎችም መምህራን ባዘጋጁት ዕቅድ መሰረት መተግበር አለመተግበራቸውን፣ መምህራን የትምህርት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ ጥረት ማድረግ አለማድረጋቸውን፣ መምህራን ዕቅዳቸውን ባቀዱት ሰአት በአግባቡ መተግበር አለመተግበራቸውን /ማጠናቀቅ አለማጠናቀቃቸውን መምህራን የሚያዘጋጁት ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊው የትምህርት ዕቅድ ጋር ተዛማጅነት ያለው መሆኑን እና ተዛማጅነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም መምህራን

ለትምህርት ማጠናከሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን እና መምህራን የዕለቱን ትምህርት አስተምረው ካገባደዱ በኋላ የዕለቱን ትምህርት መከለስ አለመከለሳቸውን ለማረጋገጥ የተዘጋጁ የምልከታ መከታተያ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተገለጸው ማብራሪያ እንደሚያሳየን የመምህራኑ የዕቅድ አተገባበር ከአዎንታዊ ጎኑ ይልቅ አሉታዊ ጎኑ የሚያመዝን ሆኖ የተገኘ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ጥናቱ በተከናወነባቸው ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚተገበሩት የትምህርት ዕቅዶች በተፈለገው መንገድ ስራ ላይ አለመዋላቸውን የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የትምህርት ዕቅዱ በአግባቡ ካልተተገበረ በአመቱ የትምህርት ወቅት መጠናቀቅ የነበረበት የትምህርት ሽፋን ሳይሸፈን ይቀራል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለትምህርቱ የተሰጠው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን አስመልክቶ በሌላው ተመሳሳይ ምድብ የቀረቡት የመከታተያ መገምገሚያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው?
2. ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች ናቸው?
3. መምህሩ ተማሪዎቹን ጥያቄ ይጠይቃሉ?ተማሪዎቹ እንዲጠይቁስ ያበረታታሉ?
4. በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት ተማሪዎች በፍላጎት ይሳተፋሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ከላይ በመጀመሪያ ለቀረበው "የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው?" ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት ከክፍል ምልከታ ከተገኘው መረጃ ሁለቱ አዎ የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ ነው  የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን ሃያ ስምንቱ ደግሞ የተማሪዎቹ የክፍል ተሳትፎ አመርቂ አይደለም፡፡ የሚል ምላሽ አስተገኝቷል፡፡ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች ናቸው? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በሁለት ምልከታ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች መሆናቸውን ሲያመለክት ሃያ ስምንቱ ምልከታ ደግሞ የሚያሳየን ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁዎች አለመሆናቸውን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው የተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ዝግጁ አለመሆን መምህራኑ አዘጋጅተው በሚተገብሩት

ዕቅድ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድርባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት የተማሪዎች ለትምህርቱ ተነሳሽነት ማጣት መምህራን ዕቅዳቸውን በተፈለገው ጊዜና ሰአት እንዳያጠናቅቁ እንቅፋት እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡

በሌላ መልኩ መምህራኑ ተማሪዎቹን ጥያቄ ይጠይቃሉ ተማሪዎቹ እንዲጠይቁስ ያበረታታሉ? ለሚለው መገምገሚያ መስፈርት በተደረገው ምልከታ ለማየት የተቻለው አስራ አራት የሚሆነው አዎ ያረታታሉ ተማሪዎቹንም ይጠይቃሉ የሚል ምላሽ ያስገኘ ሲሆን አስራ ስድስት የሚሆነው ደግሞ አይደለም ወይም አያበረታቱም ተማሪዎቹንም አይጠይቁም የሚል ምላሽ ያስገኘ ሆኗል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎቹን ጥያቄ በመጠየቅና እንዲጠይቁ የማይበረታቱ ከሆነ የተማሪዎቹ ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ የተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ተሳትፎ ደግሞ አነስተኛ መሆኑ መምህራን አዘጋጅተው በሚተገብሩት ዕቅድ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር መሆኑ የታመነ ነው፡፡ ከዚህ ምልከታም የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ይሄንኑ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ይህን በተመለከተ Dorothy (1985፡32) "ብቁ መምህራን ያለማቋረጥ ያስተማራቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩ ባዘጋጁት መሥፈርት ይመዝናሉ፡፡ መምህሩም ራሱን ይመዝናል፡፡ ይኼውም የተማሪዎችን ፍላጎት መጠበቅ አለመጠበቁን የተጠቀሙባቸው የትምህርት ማጠናከሪያዎች ተገቢ መሆናቸውን በተማሪዎቹ መካከል ባለው ልዩነት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠና በራሱና በተማሪዎቹ መካከል የነበረውን መስተጋብር በቂ መሆን አለመሆኑን ራሱን ይጠይቃል"ይላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት ተማሪዎች በፍላጎት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን ለመረዳት በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመን የሚከተለውን ነው፡፡ ከተከናወነው ሰላሳ ምለከታ ውስጥም አራቱ አዎ በፍላጎት ይሳተፋሉ የሚል ሲሆን የተቀረው ሃያ ስድስቱ ደግሞ በፍላጎት አይሳተፉም የሚል ምላሽ አስገኝቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ከላይ በሌላዎቹ ምልከታዎች እንዳየነው የተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር በፍላጎት አለመሳተፍ መምህራን በሚተገብሩት ዕቅድ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ መኖሩን አመላካች ነው፡፡

### 4.2.4. ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከመጋቢት 2008 እስከ ሚያዝያ 2008 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕለታዊ ዕቅድ አዘጋጃጀትና አተገባበር በማስመልከት ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ ትንተና፡፡

ጥያቄ አንድ፡- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ያዘጋጃሉ ? የማያዘጋጁ ከሆነ ለምን ? ለሚለው መምህራኑ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳቸውን እንደሚዘጋጁ አስሩም መምህራን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ዕቅድ አዘጋጅቶ መጠቀም እንደ ግዴታ የሚቆጠር እና አለማዘጋጀት ደግሞ የሚያስጠይቅ መሆኑን መምህራኑ በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚያነሱት በትምህርት ቤት ውስጥ መምህራን ያላቸውን የስራ አፈጻጸም ለመገምገም ከሚወጡት መስፈርቶች መካከል አንዱ መምህራን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያዘጋጁት የትምህርት ዕቅድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን በትምህርት ቤት ውስጥ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዕቅዱን የሚያዘጋጁት የስራ ግዴታ ስለ ሆነ እንጂ መከናወን ያለበት ሙያዊ ተግባር እንደሆነ የታመነበት አይመስልም፡፡

ጥያቄ ሁለት፡- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ በተፈለገው ጊዜ እንዳያዘጋጁ እንቅፋት የሚሆንቦት ነገር አለ? ካለ በዝርዝር ቢገልጹልኝ፣ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አስሩም መምህራን ዕቅዳቸውን በተፈለገው ጊዜ ለማዘጋጀት እንቅፋት የሚሆኑባቸው ምንም አይነት ነገር ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ በግላዊ ችግሮች ምክንያት ዕቅዶች ሳይታቀዱ የሚቀሩበት አጋጣሚዎች መኖራቸውን አልሸሸጉም፡፡

ጥያቄ ሦስት፡-ወደ መማሪያ ክፍል ሲሄዱ ዘወትር ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ይዘው ይገባሉ? ይዘው የሚገቡ ከሆነ ለምን ይዞ መግባት አስፈለገ ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፡፡

ከአስሩ መምህራን ለተጠየቁት ጥያቄ አራቱ ምላሻቸው አዎን የሚል ሲሆን ለምን ይዞ መግባት አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ ምክንያታዊ ምላሻቸውን በተመሳሳይ መንገድ እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

- የትምህርቱን መነሻና መድረሻ ለማወቅ ስለሚያግዘኝ
- የማስተምረውን ትምህርት በመመጠን ለተማሪዎች ለማስተላለፍ ስለሚያግዝ
- የዕለቱን ትምህርት ከየት እንደምጀምርና የት ላይ ማቆም እንዳለብኝ እንደ መሪ መሳሪያ ስለሚያገለግል
- አመታዊ ትምህርቱን በአግባቡና በተገቢው መንገድ ለማጠናቀቅ እንዲያግዝ
- መምህሩን በዕቅዱ መሰረት እንዲመራ ስለሚያግዝ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን

በአጠቃላይ አንድ መምህር ለዕለቱ ትምህርት ማስተማር ያለበትን የትምህርት ጅምርና ገደብ ማወቅ የሚችለው በመሪነት በዕቅዱ እየተመራ መተግበር ሲችል ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ዕለታዊ ዕቅዱን ዘውትር በክፍል ትግበራ ወቅት ሊገለገልበት የሚገባ መሣሪያው ስለሆነም ጭምር ነው ብለዋል፡፡

የተቀሩት ስድስት መምህራን ግን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዱን አብዛኛውን ጊዜ ወደ ክፍል ይዘው እንደማይገቡ በተመሳሳይ መልኩ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚያነሱት ዕለታዊ ዕቅዱን የምናወጣው ከትምህርት ክፍሉ እና ከትምህርት ቤቱ የስራ ሃላፊዎች የሚቀርብብንን ጥያቄ ለመመለስ ብቻ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ እና የትምህርቱ ይዘት ስፋት የማይመጣጠን በመሆኑ በዕለቱ የምናስተምረው ትምህርትና አመታዊ የትምህርት ዕቅዱ አብሮ የማይሄድ መሆኑንም በተጨማሪ አስረድተዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ዕቅዱን ወደ ክፍል ይዘን ብንገባም ዕቅዱን እያየን የማንጠቀምበት ስለሆነ ይዘን ብንገባም ይዘን ባንገባም ልዩነት የለውም ብለዋል፡፡ ይህ የሚሳየው መምህራኑ የትምህርት ዕቅዱን እምብዛም የሚገለገሉበት እንዳልሆነ ነው፡፡ እንዲህ መሆኑ ደግሞ የትምህርት እቅድ በአግባቡ እየተተገበረ እንዳልሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ዕቅድ በአግባቡ ካልተተገበረ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ወደተፈለገው አካል ማድረስ አይቻልም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ይመስላል፡፡

ጥያቄ አራት፡- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶትን ሲያዘጋጁ ስርአተ ትምህርትና የመምህሩን መምሪያ ይጠቀማሉ ? የማይጠቀሙ ከሆነ ለምን? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡

በቀረበላቸው ጥያቄ ስድስት መምህራን በዕቅድ ዝግጅታቸው ወቅት ሥርዓተ ትምህርቱን እና የመምህሩን መምሪያ የሚጠቀሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የተቀሩት አራት መምህራን ግን ምንም አይነት ሥርዓተ ትምህርትም ሆነ የመምህሩን መምሪያ እንደማይጠቀሙ ነው የተናገሩት፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚያነሱት በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙት ሁለት መምህራን በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ሥርዓተ ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ የሌለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በአሰንዳቦ እና በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሁለት መምህራን ግን ሥርዓተ ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ ያለመጠቀማቸው ምክንያት እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡ በመማር ማስተማር ስራ የረጅም ጊዜ ልምድ ያለን ስለሆነ ሥርዓተ ትምህርቱንም ሆነ የመምህሩን መምሪያ ሳንጠቀም መጥነን ማዘጋጀት ስለምንችል ነው ብለዋል፡፡ ሁሉም መምህራን እንዳሉት በትምህርት ቤቱ የመምህሩ መምሪያ ቢኖርም በመምህሩ  መምሪያ የጠቀመጠው ይዘት ከተሰጠን ክፍል ጊዜ ጋር ተጣጥሞ ስለማይሄድልን ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ለትምህርቱ የሚዘጋጀውን ዕቅድ በተፈለገው መንገድ ወደ ተግባር ለመለወጥ ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ በመምህራኑ የትምህርት ዕቅድ አተገባበር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው ይመስላል፡፡

ጥያቄ አምስት፡- የሚያዘጋጁት ዕለታዊ እቅድ ከዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር በመጣጣም በተፈለገው ጊዜ ይጠናቀቃል?  የማይጠናቀቅ ከሆነ ምክንያቱን ቢያስረዱኝ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሶስት መምህራን ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ በተፈለገው ጊዜ መጠናቀቅ እንደሚችል በተመሳሳይ መንገድ ገልጸዋል፡፡ ማጠናቀቅ የቻሉበትንም ምክንያት ሲያስረዱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ ሆኖ ሳይሆን በተጨማሪ ክፍለ ጊዜ በመታገዝ ተማሪዎቹን ለመርዳት ከመነጨ ፍላጎት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሰባት መምህራን በበኩላቸው ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ በተፈለገው ጊዜ መጠናቀቅ እንደማይችል ገልፀዋል፡፡ ለዚህ ጥያቄ በተያያዥነት የትምህርት ዕቅዱ በተፈለገው ጊዜ የማይጠናቀቅ ከሆነ ምክንያቱ ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፡፡

- ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆኑ እና ከትምህርቱ ይዘት  ጋር የማይመጣጠን መሆኑ

- የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል እና ለቋንቋው ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን የወጣውን እቅድ ከዳር ለማድረስ አዳጋች መሆኑን በተመሳሳይ መንገድ ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ ስድስት፡- የትምህርት ዕቅድን አስመልክቶ በትምህርት ቤቱ የተሰጠ ስልጠና አለ ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የትምህርት ዕቅድን በተመለከተ በትምህት ቤቱ ውስጥ የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ በአምስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙት አስሩም መምህራን ገልፀዋል፡፡ ይህ የሚያስረዳው መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለሚያቅዱትና ለሚተገብሩት የትምህርት ዕቅድ ትኩረት እንዳይሰጡ በር የከፈተ መሆኑን ነው ፡፡ በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው የትምህርት ዕቅድን በተመለከተ ከማዘጋጀትና ከመተግበር አንጻር በየዜው ስልጠና ማዘጋጀትና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የዚህ ጥናት አቅራቢ ሙሉ እምነት ነው፡፡

ጥያቄ ሰባት፡- የዕቅድ አዘገጃጀትን በተመለከተ ያሎት ግንዛቤ ምን ይመስላል ? የሚለው ጥያቄ ስለ አዘገጃጀቱ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያብራሩ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡

በቀረበላቸው ጥያቄ ስለዕቅድ አዘገጃጀት ያላቸውን ግንዛቤ አምስት መምህራን ከፍተኛ ግንዛቤ እንዳላቸውና ይህን ለማለት የቻሉበትን ምክንያት ሲገልፁ ለ10ኛ ክፍል በሚዘጋጀው ዕቅድ ላይ አንድም ጊዜ የማስተካከያ አስተያየት ስላልተሰጠን ነው ሲሉ መልሰዋል፡፡ በተጨማሪም የምህርነት ስልጠና ከመውሰዳችን በተጨማሪ ሙያችን ስለሆነ የተሻለ ግንዛቤ አለን ብለዋል፡፡ በሌሎቹ ተደልድለው የሚያስተምሩት አምስት መምህራን ደግሞ የዕቅድ አዘገጃጀትን በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ መጠነኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው በዕቅድ ዝግጅታቸው ዙሪያ አልፎ አልፎ ከትምህርት ክፍሉ አስተያየት ተሰጥቶን ማስተካከያ ስናደርግ ስለነበረ ነው ብለዋል፡፡

ጥያቄ ስምንት፡-. በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚሰጡትን የክፍል ሥራዎችንና የቤት ስራዎችን ተከታትለው ያርማሉ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡

በቀረበላቸው ጥያቄ አምስት መምህራን ለተማሪዎቹ የተሰጡትን ተግባራት በትርፍ ጊዜያቸው ተከታትለው እንደሚያርሙላቸው ሲናገሩ የተቀሩት አምስቱ ግን ተከታትለው ለማረም እንደማይችሉ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚያነሱት አንድ መምህራኖቹ ሲገልጹ፡-

- የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ይህን ተግባር ለማከናወን ስለማያስችለኝ እና ወደኋላ ስለሚያስቀረኝ እና የትምህርቱን ይዘት ለማካለል ተጽዕኖ ሰለሚፈጥርብኝ
- የተማሪዎቹ በአንድ ክፍል ውስጥ ከሚፈለገው ቁጥር በላይ መብዛቱ አሰልቺ መሆኑ
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተሰጠኝ ተደራራቢ ስራ በመኖሩ በትርፍ ጊዜዬ አንኳን ለማረም አላስቻለኝም የሚል ተቀራራቢ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ ዘጠኝ፡- የክፍል ሥራዎቹና የቤት ሥራዎች ታቅደው ይሰጣሉ? የማይሰጡ ከሆነ ለምን? ለሚለው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በቀረበላቸው ጥያቄ አምስት መምህራን የክፍል ሥራዎቹና የቤት ሥራዎች ታቅደው ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ አዎ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት አምስቱ ግን የክፍል ሥራዎቹና የቤት ሥራዎች ታቅደው የማይሰጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የማይሰጡበትን ምክንያት እንዲገልጹ ለቀረበላቸው ተከታታይ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡-

- የተማሪዎቹ ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑ
- ተማሪዎቹ አብዛኛውን ጊዜ የተሰጣቸውን ስራዎች በአግባቡ ስለማይተገብሩ
- ተማሪዎቹ የክፍል እና የቤት ስራዎቹን ሰርተው ለማሳየትና ሰርተው ለመምጣት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑ እና
- ከተማሪዎቹ ብዛት አንጻር ለማረም አዳጋች ስለሚሆን እንዲሁ በዘፈቀደ የሚሰጡ ናቸው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ አስር፡-በክፍለ ጊዜዎት የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ተቀራራቢ የሆነ ተሳትፎ ይኖራቸዋል ? ከሌላቸው ምክንያቱ ምንድነው?

ለሚለው ጥያቄ አስሩም መምህራን ለተጠየቁት ጥያቄ በክፍል ውስጥ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ተቀራራቢ የሆነ ተሳትፎ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚያነሱት የሚከተለውን ነው፡፡

- የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ስላለባቸው
- የአማርኛ ቋንቋን የሚማሩት ከአምስተኛ ክፍል ተነስተው መሆኑ
- የአማርኛን ቋንቋ ከሌላው የትምህርት አይነት ጋር እኩል ስለማያዩት ያላቸው የትምህርቱ ተሳትፎአቸው መመጣጠን እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡
- አማርኛ ቋንቋን ስለማይችሉ፤

- የትምህርቱ ይዘት ከእውቀት ደረጃቸው በላይ በመሆኑ፤
- ተማሪዎቹ የተለያየ ዳራዊ እውቀት ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ በመሆናቸው
- የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል እና ተሳትፎ እኩል ባለመሆኑ
- የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው
- ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ እና እንደ ተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ችሎታ መለያየት የተነሳ ሁሉም ተማሪዎች አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ያስተማሩትን ትምህርት እኩል እንደማይረዱ ገልጸዋል፡፡

ከላይ እንደተረዳነው የተማሪዎች የዕውቀት ደረጃ ተመጣጣኝ አለመሆን በትምህርት ዕቅዱ አዘገጃጀት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር መቻሉን ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የትምህርት ዕቅድ መርህ ሐሰቦችን አጠናክሮ በቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገገጃጀት ላይ በትክክል ለማስፈር ተፅእኖ ያመጣሉ የሚሏቸውን Musica (1991፡421-422) እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል፡፡ በትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ላይ በመሠረታዊነት ደረጃ ተፅእኖ ሊያመጡ ከሚችሉት ጉዳዮች አንዱ ጊዜ ነው፡፡ ይህም የመንፈቀ ዓመቱን ሁኔታ፣ ማለትም የክፍል ጊዜውን ድግግሞሽ እና እርዝማኔ የተመለከተ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው የተማሪዎች የዕውቀት ደረጃ ተመጣጣኝ መሆኑንና አለመሆኑን ይመለከታል፡፡ ይህም በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የዕውቀት ወይም የችሎታ ልዩነት መጠኑ ምን ያህል ነው የሚለውን ይመለከታል፡፡ ሌላው የተማሪዎቹ ልዩነት በዕድሜ ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ለትምህርት ባላቸው ፍላጎት እና የተማሪዎችን ግላዊ ሁኔታ ይጨምራል፡፡ በመጨረሻም ስለትምህርቱ ቀደም ሲል ያላቸውን እውቀትና ግንዛቤ በዕቅዱ አዘጋጃጀት መርህ ግብር ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይላሉ ይህ የሚስረዳው ከላይ ለተነሱት ጥያቄዎች በምክንያትነት የተሰነዘሩት ሃሳቦች በዕቅድ አዘገጃጀቱና አተገባበሩ ላይ የሚያሰድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከተጠኚዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ያስተማሩትን ትምህርት እኩል እንደማይረዱ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ምክንያት ሁሉም ተማሪዎች

አንድ ወጥ በሆነ መልኩ መምህሩ ያስተማሩትን ትምህርት በተቀራራቢነት የማይረዱ ከሆነ መምህራን ያቀዱትን ዕቅድ በአግባቡ ለመተግበር እና በታቀደው ክፍለ ጊዜ ማጠናቀቅ ላያስችላቸው ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ ምክንያቱም የትምህርቱን ሂደት በተፈለገው መንገድ እንዳያስኬዱት በትምህርት አቀባበላቸው ወደ ኋላ የሚቀሩ ተማሪዎች ተጽዕኖ ያሳድሩባቸዋል፡፡

ጥያቄ አስራ አንድ፡-የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በየጊዜው የክፍል ምልከታ ይከናወናል? ከተከናወነ በአመት ውስጥ ስንት ጊዜ ይከናወናል? የማይከናወን ከሆነስ ምክንያቱ ምንድነው?

ከላይ በተመለከተው ጥያቄ አንድ ላይ የተሰጠው ምላሽ በአምስቱም ትምህርት ቤት ያሉት የአማርኛ ቋንቋ ሁሉም መምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በየጊዜው የክፍል ውስጥ ምልከታ መከናወኑን በአዎንታ መልሰዋል፡፡ ምልከታው የሚከናወን ከሆነ በአመት ስንት ጊዜ እንደሚከናወን ለቀረበላቸው ተከታይ ጥያቄ እንዲህ በማለት መልሰዋል፡፡ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ሁለት መምህራን በአመት አራት ጊዜ ምልከታ እንደሚደረግላቸው ሲገልጹ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የተቀሩት ስምንት መምህራን ግን በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ምልከታው እንደሚከናወን ገልጸዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው  በዕለታዊ ዕቅዱ አዘገጃጀትም ሆነ አተገባበር ዙሪያ አስፈላጊና በቂ የሆነ ክትትል የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በየጊዜው ታቅደው ወደ ተግባር የሚሸጋገሩት ዕቅዶች አተገባበራቸው ላይ ክትትል እና ድጋፍ አለማድረግ የሚፈለገውን ግብ ያሳካል ማለት አዳጋች ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚተገበሩት የቋንቋው እቅድ በአመት ውስጥ ቢያንስ አራት ጊዜ አልያም ስድስት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግላቸው አመርቂ ውጤት ሊገኝ ይችላል ብሎ ያምናል፡፡

ጥያቄ አስራ ሁለት፡-. የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተከናወነ በኋላ በቂ የሆነ ገንቢ አስተያት ይሰጣል?

ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተከናወነ በኋላ በቂ የሆነ ገንቢ አስተያየት ይሰጣል? ለሚለው ጥያቄ ስምንት መምህራን ገንቢ አስተያየት ከክፍል ምልከታ በኋላ እንደሚሰጣቸው ሲገልፁ የተቀሩት ሁለቱ መምህራን ግን ምንም አይነት አስተያት

ተሰጥቶን አያውቅም ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ በጥያቄ አስራ አንድ ላይ እንደተመለከትነው በአመት ውስጥ የሚከናወነው የዕቅድ አተገባበር ምልከታ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የሚከናወነው ምልከታ አነስተኛ በመሆኑ የሚሰጠው አስተያየት በቂ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ እንደሆነ የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ነው፡፡

ጥያቄ አስራ ሶስት፡- ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንጻር በቂ ነው ብለው ያስባሉ? ካልሆነ ምን መሆን አለበት ይላሉ?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት መምህራን ሁላቸውም ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንጻር በቂ አይደለም የሚል ምላሽ ነው የሰጡት፡፡ ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንጻር በቂ አይደለም ካሉ ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ? ለሚለው ጥያቄ የየራሳቸውን ምክንያታዊ ምላሽ በሚከተለው መልክ መልሰዋል፡፡

- ለትምህርቱ የተሰጠውን ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ መጨመር
- ተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀታቸው እንዲሻሻል የአማርኛ ቋንቋን ከአንደኛ ክፍል ጀምረው እንዲማሩ ቢደረግ
- ከተቻለ ሳምንታዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜውን መጨመር ካልሆነም የመጽሐፉን የትምህርት ይዘት መቀነስ
- ተማሪዎቹን በተጨማሪ የትምህርት ጊዜ መርዳት ማለትም ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጪ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚሉትን ሃሳቦች በመጥቀስ ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ጥያቄና ከተሰጠው ምላሽ የምንረዳው መምህራኑ ያቀዱትን ዕቅድ በተፈለገው ጊዜና ባቀዱት መሰረት ለመተግበር ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም መምህራኑ በምክንያታዊ ምላሻቸው የሰነዘሩት ሃሳብ ሊተኮርበት እንደሚገባ የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት መሆኑን መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

ጥያቄ አስራ አራት፡- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ለመማር ያላቸው ዝግጁነት ምን ይመስላል?

በጥያቄ አስራ አራት ለተነሳው ጥያቄ መምህራኖቹ የሰጡት ምላሽ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ለመማር ያላቸው ዝግጁነት ከፍተኛ መሆኑን አንድ መምህር አስረድተዋል፡፡ የተቀሩት ዘጠኝ መምህራን ግን ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ

ትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመማር ያላቸው ዝግጁነት ዝቅተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል ተብለው ተጨማሪ ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ በብዛት በአካባቢያቸው ቋንቋ የሚጠቀሙ በመሆኑና አማርኛን ቢያውቁትም ባያውቁትም ብዙም የሚጠቅማቸው ስለማይመስላቸው ይመስለናል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከጥያቄ አንድ እስከ ጥያቄ አስራ አራት ድረስ ለመምህራን የቀረበላቸው ጥያቄ የዕቅድ አዘገጃጀትን እና አተገባበርን ለመፈተሽ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራኖቹ የመለሷቸው ምላሾች የሚያሳየው የሚታቀደውን ዕቅድ በተፈለገው መንገድ ለመተግበር ችግሮች እንዳሉባቸው የሚያመላክት ነው፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆን፣ የተማሪዎቹ ቋንቋውን የመማር ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ ተማሪዎቹ ትምህርቱን የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ ከተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት ጋር አለመመጣጠን፣ የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸውን ዝንባሌ የቀነሰባቸው መሆኑን በአጽንኦት የተነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

### 4.2.5. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት አቅርቦት ዘዴ

የመማር ማስተማር ዘዴዎች በመምህሩና በተማሪው መካከል እንደመገናኛ ድልድይ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ዘዴዎቹ የመማር ማስተማሩን የትምህርት ዓላማን ማስፈፀም የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ እነኚህ ዘዴዎች እንደ ትምህርት ሁኔታ የመለዋወጥ ባህሪይ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ አንድ ወጥ የሆነ ዘዴን ሁልጊዜ መጠቀም በተማሪዎች ላይ መሰላቸትን ከመፍጠሩም ባሻገር ትምህርቱን በንቃት እንዳይከታተሉ ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዘዴዎቹ በትምህርት ሂደት መምህሩ የሚያስተምረውን ትምህርት ባቀደውና በፈለገው ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ሲባል ትምህርቱ የሚሰጠው በጊዜ ላይ ተመርኩዞ ስለሆነ የሚነደፈው የትምህርት ይዘትም ሆነ አላማ በታቀደው ጊዜ መጠናቀቅ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህ ሳይሆን ከቀረ አልፎ አልፎ በክፍል ምልከታ እንደተስተዋለው የተጀመረው ትምህርት በወቅቱ ሳይጠናቀቅ የመቅረት ዕድል ይገጥመዋል፡፡ በመሆኑም መምህራኑ የትኛው ዘዴ ከየትኛው ትምህርት አላማ ጋር ሊሄድ ይችላል የሚለውን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ ሲባል በሁሉም መምህራን በኩል ችግሩ ይስተዋላል ማለት ሳይሆን ችግሩ ጎልቶ የሚታይባቸው መምህራን ለትምህርቱ የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ እጥረት በማየት ብቻ የትምህርቱን ሽፋን ለማጠናቀቅ መሞከር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ሌሎች አማራጮችን ለመጠቀም መሞከር እንዳለባቸው ለመጠቆም ነው፡፡

### 4.2.5.1. የመምህራኑና የተማሪው ተራክቦ

ከምልከታው ለመረዳት እንደተቻለው አሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ አንድ መምህር  ከተማሪዎቹ ጋር የነበራቸው መስተጋብር ከሌሎች  ክፍሎች ሁሉ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም መምህሩ ለተማሪዎቹ አጠር ያለ ቀልድ በመናገር አነቃቅተው ተማሪዎቹ በቡድን አደራጅተው የሚያስተምሩ በመሆኑ የተማሪዎቹ ለትምህርት መነቃቃት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከተደረገው ምልከታ እንደምናስተውለው በአብዛኛው ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ መልስ በመስጠት በቡድን ተከፋፍለው ሃሳባቸውን በመግለፅና የመሳሰሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ታስቦ የተዘጋጀ እቅድ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ይህ የዕቅድ አዘገጃጀት ስልት በተማሪዎቹና በመምህራኑ መካከል ያለው የመማር ማስተማር ግንኙነት የተሻለ ደረጃ ላይ ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ ዕቅዱ በአብዛኛው በታቀደው መልኩ ያልተተገበረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በምህራኑና በተማሪዎቹ መካከል የነበረው መስተጋብር አመርቂ ነው ብሎ መደምደም አልተቻለም፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው አንድም ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው መነሳሳት አነስተኛ መሆንና ፍላጎት ማጣት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት በዚህ ጥናት አቅረቢ ላይ አሳድሯል፡፡ ይህን በተመለከተ የዚህ ጥናት አቅራቢ የተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት ምን እንደሆነ ሌላ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል፡፡

### 4.2.5.2 የትምህርት ዕቅድ ግምገማ

ግምገማ የመማር ማስተማር ሂደት ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ እገዛ የሚያደርግልን ሂደት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ መምህሩ ተግባሩ ምን ያህል እንደተሳካ ራሱን የሚፈትሽበትና ተማሪው ምን ያህል እወቀት እንደጨበጠና እንደተለወጠ ራሱን  የሚገመግምበት  መንገድ በመሆኑ ለሁለቱም ወገን ያለው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Dorothy (1985፡32) “ብቁ መምህራን ያለማቋረጥ ያስተማራቸውን ተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩ

ባዘጋጁት መሥፈርት ይመዝናሉ፡፡ መምህሩም ራሱን ይመዝናል፡፡ ይኼውም የተማሪዎችን ፍላጎት መጠበቅ አለመጠበቁን የተጠቀሙባቸው የትምህርት ማጠናከሪያዎች ተገቢ መሆናቸውን በተማሪዎቹ መካከል ባለው ልዩነት ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠና በራሱና በተማሪዎቹ መካከል የነበረውን መስተጋብር በቂ መሆን አለመሆኑን ራሱን ይጠይቃል"ይላሉ፡፡ይህ ማለት ለመማር ማስተማር ሂደት በነደፈው የትምህርት ዕቅድ መሠረት የታለመው የትምህርት ዓላማ በትምህርቱ ሂደት ለተማሪው መድረሱንና አለመደረሱን ማወቂያው መንገድ የተለያዩ የመመዘኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ መልመጃዎችን በማሠራት፣ በተለያዩ ጊዜያት የሙከራ ፈተናዎችን በመስጠት ተማሪዎቹ ምን ያል የባህርይ ለውጥ እንዳመጡ ለመገምገም የሚረዳው ስልት ነው፡፡

በመሆኑም መምህራኑ በዕለታዊ ዕቅዳቸው ላይ ለግምገማ ያቀዱት መልመጃ ማሰራት፣ ጥያቄ መጠየቅ የቡድን ስራ መገምገም ብለው ያሰፈሩትን ለመተግበር ጥረት ሲያደርጉ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በገበሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተደልድለው የሚያሰስተምሩ መምህራን ቋንቋውን የሚያስተምሩት በንዑስ የትምህርት ዘርፍነት በመሆኑና በኦሞናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ አንድ መምህር ግን ከትምህርታቸው ይዘት ሰፋት አንፃር የግምገማ ተግባር ለማከናወን የሰዓት እጥረት እንዳጋጠማቸው አጥኚው ተረድቷል፡፡

ይህን በተመለከተ ከድህረ ገጽ የተገኘው መረጃ እንዲህ ይላል፡፡ ይህ ክፍል ተማሪዎች የተማሩትን ወደ ተግባር እንዲያሸጋግሩ የሚደረግበትና በዚህም ጥረት ዉስጥ ብቃታቸዉ የሚፈተሸበት ክፍል ነዉ፡፡ በእለታዊ የትምህርት እቅድ ዉስጥም መምህሩ ተማሪዎቹን እንዴት ወደ ትግረበራ መምራት እንደሚችል በግልፅ ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር htt;/www.crit.umich.edu/gsis/Pg-1.php በተዘጋጀዉ ዕለታዊ እቅድ ውስጥ ግምገማ ማድረግ ተማሪዎቹ የሚያሳዩት የግብረገብ እንቅስቃሴ የማስገንዘብ ብቃት ይኖረዋል ይላል፡፡ በመሆኑም የታቀደው ዕቅድ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚቻለው ተማሪዎቹ በታቀደው መሰረት ለግምገማ የተቀመጠውን ፅንሰ-ሀሳብ መረዳታቸውን ሲረጋገጥ መሆኑን የሚያስገነዝብ ይመስላል፡፡

## ምእራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች

ይህ ምእራፍ በምእራፍ አራት ላይ የተተነተነውን የጥናቱን ክፍል መሰረት በማድረግ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡ ጥናቱ ቀደም ባሉ ምእራፎች እንደተገለጸው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ እና በኦሞ ናዳ ወረዳ በሚገኙ በተመረጡ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትን አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽና ዕቅዱን ከማዘጋጀትና ከመተግበር አንጻር  የሚያጋጥሙ ችግሮችን መተንተን ነው፡፡

ጥናቱ በተለይ በአስረኛ ክፍል ውስጥ ተደልድለው የሚያስተምሩ መምህራን የሚያዘጋጁአቸውን ዕቅዶች በመፈተሽ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ጥናቱ የሚመልሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎችም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን ይመስላል? በዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምንድን ናቸው? ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ጋር እኩል ተጣጥሞ መጠናቀቅ ይችላል? የሚሉ ናቸው፡፡

አጥኚው ይህን ጥናት ከዳር ለማድረስ ከጥናቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነትና ቀረቤታ ያላቸውን የተለያዩ መጽሓፍት በመጠቀም ባገኛቸው መረጃዎች ክለሳ ድርሳናቱን አጠናክሯል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ወቅት መምህራን ሊተገብሯቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮችም በክለሳ ድርሳናቱ ተካተዋል፡፡

አጥኚው ገላጭ የምርምር አይነትን የተጠቀመ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ሲል በክፍል ውስጥ ምልከታ ፣ በቃል መጠይቅ እና  በሰነድ ፍተሻ የሰበሰባቸውን መረጃዎች በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅሞ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ትንታኔው ከተካሄደ በኋላ የሚከተሉት የማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በቃል መጠይቅ እና በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች እንደሚገልጹት ከሆነ የአማርና ቋንቋ መምህራን የሚያዘጋጁአቸውና የሚተገብሯቸው ዕቅዶች በተፈለገው ወቅት እንዳይጠናቀቅ የሚያስቸግሯቸው ነገሮች እንዳሉ መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህ መሰረት የተገኘው መረጃ እንደሚገልጸው ከሆነ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ የተለያዩ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ከአንድ አላማ በላይ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ማቀድ፣ ለክፍለ ጊዜው ይመጥናል ተብሎ የታቀደው ዕቅድ በአግባቡ ተተግብሮ አለመጠናቀቅ፣ መምህራን ባቀዱት ዕቅድ መሰረት እንዳይተገብሩ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ በአንድ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ ከሚችል በላይ ሰፊ የሆነ ይዘት ይዞ ወደ መማሪያ ክፍል መግባት (ይዘትና ዓላማን አለመመጠን)፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎቻቸው ተለዋዋጭ አለመሆን እና በዕቅዱ ውስጥ ለትግበራ የተቀመጡት የአተገባበር ሂደቶች በታቀደው ዕቅድ መሰረት አለመተግበራቸውና የመሳሰሉት ይገኙበታል ፡፡

ከመምህራን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራን ወደ መማሪያ ክፍል ሲሄዱ ዘወትር ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ይዘው እንደሚገቡ፣ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ በተፈለገው ጊዜ እንዳያዘጋጁ እንቅፋት የሚሆንባቸው ነገር እንደሌለ፣ የትምህርት ዕቅድን አስመልክቶ በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ፣ የሚያዘጋጁት ዕለታዊ እቅድ ከዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር በመጣጣም በተፈለገው ጊዜ የማይጠናቀቅ መሆኑን፣ ለዚህም በምክንያትነት የሚያነሱት ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆኑ እና ከትምህርቱ ይዘት ጋር የማይመጣጠን መሆኑ የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል እና ለቋንቋው ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን የወጣውን እቅድ ከዳር ለማድረስ አዳጋች መሆኑን በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡

በክፍለ ጊዜያቸው የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ያላቸው ተሳትፎ ተቀራራቢ አለመሆን መጠይቁ ከቀረበላቸው አስሩ መምህራን ሰባቱ ማጠናቀቅ እንደማይችሉ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚነሱት ሃሳቦች የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ያለባቸው መሆኑ፣ የአማርኛ ቋንቋን የሚማሩት

ከአምስተኛ ክፍል ጀምረው መሆኑ፣ ተማሪዎቹ የተለያየ ዳራዊ እውቀት ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ በመሆናቸው፣ የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል እና ተሳትፎ እኩል ባለመሆኑ፣ የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው፣ የአማርኛን ቋንቋ ከሌላው የትምህርት አይነት ጋር እኩል ስለማያዩት ያላቸው የትምህርት ተሳትፎ መመጣጠን እንዳልቻለ፣ ለትምህርቱ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንጻር በቂ አለመሆኑን እና ዕቅዱን በተፈለገው መልኩ መተግበር እንዳልተቻለ ከጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ የሚያሳየን ደግሞ በሁሉም  አስረኛ ክፍል ተደልድለው የሚያስተምሩ መምህራን የሚያዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች የትምህርት ቤቱንና የመምህሩን ስም፣ የትምህርት ዓይነት፣ ክፍል፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን፣ የትምህርቱ ርዕስ፣ የትምህርቱ ዓላማ፣ የክፍለ ጊዜው ርዝመት፣ የርዕሱ ዝርዝር ተግባር፣ የመምህሩና የተማሪው ተግባር፣ የክፍል አደረጃጀት፣ ክትትል ግምገማና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ያካተተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዕለታዊ ዕቅድ ማቅረቢያው ቅጽ ይህን ይዘት ቢኖረውም ከቅርጽ አንጻር ስንመለከተው  ግን ልዩነቶች ይታዩበታል፡፡ በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በሳምንት ሁለት ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚዘጋጁት ዕቅዶች በአንድ ወረቀት ላይ ለሁለት ቀናት ተከፍሎ መቀመጡ ተስተውሏል፡፡ ይህ የዕቅድ አዘገጃጀት ደግሞ የሚታቀደውን ዕቅድ ግልጽ በሆነና አቅጣጫን በአግባቡ የሚጠቁም እንዳልነበረ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

በይዘት ስር የሚጠቀሱት የቃላት አጠቃቀም ግልጽነት ማጣት፣ በአላማ ስር ከተቀመጠው ሃሳብ ውጪ ተጨማሪ አላማ በሌላ ክፍለ ጊዜ መማር ያለባቸውን በመደረብ ማስተማር፣ በታቀደው እቅድ አለመመራትና ከታቀደው እቅድ ውጪ ማስተማር እና በየትምህርት ቤቶቹ የሚዘጋጁት የዕቅድ ማቅረቢያ ቅጾች የተለያየ የቅርጽ ይዘት ያላቸው መሆኑን ከታዩት የሰነድ ፍተሻ በጥናቱ የተደረሰባቸው ናቸው፡፡

ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ከአመታዊ የትምህርት ዕቅድ ይልቅ ዝርዝር ርዕስ ጉዳይን የሚይዙ መሆናቸው ከዚህ በተጨማሪ በዕለታዊ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት መነደፍ የሚገባቸው አላማዎች ውስንና ግልፅ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑና ተማሪዎችን በቀላሉ

ለመገምገም የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው ተመራማሪዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህን እንጂ በሁሉም ክፍሎች በተዘጋጁት ዕለታዊ ዕቅዶች ውስጥ የትምህርቱ ዓላማ ውስን ቢሆንም በናዳና በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁለት መምህራን ያዘጋጇቸው ሁለት ዕቅዶች አላማ ሁለት እና ከዚያ በላይ  በመሆኑ የተማሪዎቹን የባህሪይ ለውጥና ደረጃ በቀላሉ ለመገምገም የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሃሳቦች ተቀምጠዋል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኚው ባደረገው ጥናት የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ ያላቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ለመግለጽ ሞክሯል፡፡

- መምህራን በሚያዘጋጁአቸው የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የሚነድፏቸው የትምህርት ዓላማና ይዘቶች ውስንና በአንድ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ የሚችል ሆኖ ቢዘጋጅ፤
- መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርትን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያስችልና ተማሪን በንቃት ሊያሳትፍ የሚችል ተለዋዋጭ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴን ለመጠቀም የዕቅድ አዘገጃጀታቸውን ተለዋዋጭ ቢያደርጉ፤
- የአማርኛ ቋንቋን ዕቅድ አዘገጃጀትን እና አተገባበርን በተመለከተ ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ የሆነ ስልጠና በየጊዜው እያዘጋጁ ለመምህራን ቢሰጡ፤
- ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚማሩት ከአምስተኛ ክፍል ጀምረው መሆኑ ይታወቃል፤ ይህ ደግሞ መምህራን የሚያዘጋጁትን ዕቅድ በአግባቡ እንዳይተገብሩ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተማሪዎቹ ቋንቋውን የሚጀምሩበትን ክፍል ዝቅ እንዲል ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ፤
- ተማሪዎቹ ለቋንቋው ያላቸው ግንዛቤና የአማርኛ ቋንቋን ትኩረት እንዳያደርጉበት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው አካላት አልፎ አልፎ መኖራቸው ተገቢ ባለመሆኑ በሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገድ ቢመቻች፤
- መምህራን ትምህርቱን የሚያቅዱባቸው የዕቅድ ቅጾች በሁሉም ትምህርት ቤቶች ማለት ይቻላል ተመሳሳይ አይደሉም፤ ይህ መሆኑ ደግሞ የዕቅዱን አዘገጃጀትና

አተገባበር ሁኔታ የተለያየ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ መምህራን የሚያዘጋጁት የዕቅድ ቅጾች ተመሳሳይና ወጥ ሆኖ እንዲዘጋጅ ቢደረግ፤

❖ የዚህ ጥናት አቅራቢ የተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት ምን እንደሆነ ሌላ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል፡፡ የሚሉትን የመፍትሔ ሃሳቦች በመስጠት ጥናታዊ ስራው ተጠናቋል፡፡

# ዋቢ መፅሐፍት


አለም እሸቱ፡፡ (1997)፡፡ <u>መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ</u>፡፡ ኮመርሻል ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኮከቤ መኮንን (2002) የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር በወንምበራ ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፡፡ ያልታተመ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ያለው እንዳወቀ ሙሉ፡፡ (2006 )፡፡ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር</u>፡፡ አዲስ አበባ አልፋ አታሚዎች

Lewey, A. (1977), Hand book of curriculum, New York, Longman Inc.

Borich, G.D.(1988). Effective Teaching Methods (3rd ed.) Englewoo Cliffs: Printice-Hall, Inc.

Calce, Musica. M,ed (1991). Teaching English Language. New York, Longman publishing.

Callhan, J.F.and Clark,L.H.(1988).Teaching in the Middle and Secondary Schools Planning for Competence. 3rd ed.New York, Macmillan Publishing Company.

Clarc, L.Kl and stars, (1996). Second and Middle school Teaching Methods. (3rd ed.).london: upperseddle (N.J) prentice-hall. Inc.

Cross,D.(1995). Apractical Hand book of Language Teaching. London:Cassell Villiers house.

Cunning Worth,A. (1995). Choosing your Course Book. Oxford,Oxfored University press.

Dorothy, R. (1985). Teaching Elementary Language. Canada.

Dr. Bob kizlik http//www.adprima.com/mistaks.htm

Dubin, F. and Olishtain, E. (1986). Course Design. Cambridge, Cambridge University press.

Elizzabeth,P. (1982). Effective Teaching apractical Guide to Improve Teaching. New York, Longman.

Fink,Dl.(2005).http;//ida edtl. Org/wp.content /up.loads/2014/11/idea paper 42.pdf

Hargreaves, D.H. (1972). Interpersonal relation and education. London: Routledge and Kagan paul.

Harmer, J. (1991). The practice of English Language Teaching. (New edition). New York,Longman publishing.

Hay wood, John.(1982). Pitfalls planning students Teaching. New York, Nichols pit falls publishing company.

htt;//www.adprima.com/w/05.htm. the Madeline Hunter lesson Design model.

http;//gsi.berkely edu/gsi-guide-contents/ pre —semester-intro / first-day-plan

htt;/www.crit.umich.edu/gsis/Pg-1.php

Neville Grant (1991). Making the most of your text book. New York, Longman publishing.

Nunun,D. (1988). Syllabus Design. Oxford,Oxfored University press.

Sells, D. (1981). Learning and visual communication. New York John Wiley and Jons.

Seyum Tefera and Ayalew Shibeshi (1989). Fendamentals of Educational Research for Students and Begning Researcher. Addis Abeba University.

Strategies to Extend Student Thinking htt:/www.crt.umich.edu/gsis/p4 4.php.

Yalden, J.(1987). Principle of Course Design for Language Teching. Cambridge. Cambridge Cup.

Wilcox, Ray T. (1969). Effective Teaching In Ethiopia Schools. Addis Ababa. Artistic printing press.